# የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአፈጻጸም መመሪያ

## ሁሉም መንገዶች ወደ ጤና ኤክስቴንሽን ያመራሉ!

ፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚ/ር
የካቲት 1999 ዓ.ም
አዲስ አበባ

| ተ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | *መግቢያ* ..................................................................................... | 1 |
| 2 | ትርጓሜ ..................................................................................... | 4 |
| 3 | *የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዓላማ* ................................... | 5 |
| 4 | የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአፈጻጸም ስልቶች........................ | 6 |
| 5 | የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አደረጃጀት፣ የሥራ ተግባርና ኃላፊነት........................................................... | 7 |
| | 5.1. የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት ........... | 8 |
| | 5.2. የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት ....................... | 9 |
| | 5.3. የዞን ጤና መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት ........................... | 10 |
| | 5.4. የወረዳ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት ....................... | 11 |
| | 5.5. የወረዳ/የልዩ ወረዳ/ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት .... | 12 |
| | 5.6. የጤና ጣቢያ ወይም የአስኳል ጤና ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት | 14 |
| | 5.7. የቀበሌ አስተዳድር ተግባርና ኃላፊነት ................................ | 14 |
| | 5.8. የጤና ኬላ /የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ተግባርና ኃላፊነት . | 15 |
| | 5.9. የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት | 19 |
| | 5.10. የሞዴል ቤተሰብ ተግባርና ኃላፊነት ............................ | 20 |
| | 5.11. የሕብረተሰቡ ተግባርና ኃላፊነት ...................................... | 21 |
| | 5.12 የት/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት............................................ | 21 |
| | 5.13. የብዙኃን ማህበራት ተግባርና ኃላፊነት................................ | 23 |
| | 5.14. የአጋር ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት .............................. | 24 |
| 6 | በቀበሌ ደረጃ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአተገባበር ሂደት .. | 25 |
| | 6.1. መርሆዎችን መከተልና በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ላይ ስምምነት መድረስ ........................................................... | 25 |
| | 6.2. *ሞዴል የቤተሰብ ፓኬጅ የትግበራ ሂደት* ........................ | 27 |
| | 6.3. ሕብረተሰብ አቀፍ ፓኬጅን ስለማጠናከር............................. | 39 |
| | 6.4. ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሰራተኞች ጋር አብሮ ስለመሥራት..................................................................... | 40 |
| | 6.5. የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሥራ ስምሪት .................. | 46 |
| 7 | በቀበሌ ደረጃ ቅንጅታዊ አሠራር.................…...................... | 50 |
| 8 | የግብዓት አቅርቦት ሥርዓትን ስለማደራጀት.............................. | 51 |
| 9 | የሕሙማን አቀባበልና አላላክ ሥርዓት .................................... | 54 |
| 10 | ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ቀጣይነትን ስለማረጋገጥ...……….. | 56 |
| 11 | የጤና ኤክስቴንሽን ስራዎች ተፈፃሚነት ደረጃና መለኪያዎች . . | 62 |
| 12 | የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የትግበራ ፍሰት......................... | 67 |

## 1. መግቢያ

ሀገራችን ሰማንያ ከመቶ በላይ የሚሆነው ሕዝብ በገጠር በተበታተነ አሰፋፈር የሚኖርባት፣ በወሊድና ከወሊድ ጋር በተያያዙ የጤና ችግሮች የእናቶችና የሕፃናት ሞት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰባትና የነበሩት የጤና ተቋማትም በአብዛኛው በከተሞች አካባቢ ብቻ የተከማቹባት እንደሆነች ነበራዊ ሁኔታዎች ያሳያሉ፡፡

በመሆኑም ችግሮቹን ለመቅረፍ፣ በኢትዮጵያ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማምጣትና ድህነትን ለመቀነስ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀርጸው ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ በዋናነት በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረው የጤና ፖሊሲም ጤናማ ዜጋ የማፍራት ዘላቂ ግቡ እንደተጠበቀ ሆኖ ፈጣንና ቀጣይ ዕድገት ለማምጣት በሚደረገው ጥረትም ጉልህ ሥፍራ ያለው ነው፡፡ በመሆኑም የጤና ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ የጤና ልማት መርሃ ግብር ተቀረጾና በተለይ ከጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እርቆ የሚገኘውን የገጠሩን ሕብረተሰብ በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ተጠቃሚ ለማድረግ ታልሞ በስፋት በመተግበር ላይ ነው፡፡

በገጠሩ ሕብረተሰብ ዘንድ የመሰረተ ጤና ክብካቤን ማስፋፋት ተመራጩና አዋጪ ዘዴ በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በአዲስ አደረጃጀትና አወቃቀር ተዘርግቷል፡፡የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ዋና ትኩረት ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማሕበረሰብ በመሆኑ ይኸው አካል ለራሱ የጤና ጉዳይ ራሱ ኃላፊ ሆኖ በሽታን በመከላከል

ጤናማ ኑሮ እንዲመራና ምርታማ እንዲሆን ማስቻል ነው፡፡

በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ቀበሌ በአማካይ ለአምስት ሺህ ሕዝብ አንድ የጤና ኬላ በማደራጀት በሽታን በመከላከልና ጤናን በማበልፀግ ማህበረሰብና ቤተሰብ ተኮር መሠረታዊ የጤና አገልግሎቶች በመሰጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ለአምስት የጤና ኬላዎች አንድ ጤና ጣቢያ ወይም አስኳል ጤና ጣቢያ በማደራጀት ለሃያ አምስት ሺህ ሕዝብ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ይሰጣል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ ከየቀበሌው የተመለመሉ አስረኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ሴቶች በተመረጡ 16 የጤና ፖኬጆች ላይ ለአንድ ዓመት ሥልጠና ከወሰዱ በኋላ በየጤና ኬላው ሁለት ሁለት ሆነው እንዲመደቡ ተደርጓል፡፡ የእነዚህ ሠራተኞች ዋና ተግባር በሽታን በመከላከል ጤናማነትን የማጎልበት መንፈስ እንዲሰፍን ማስቻል ነው፡፡ የጤና አክስቴንሽን ሠራተኞች ሴቶች ብቻ የሆኑበት ምክንያትም የቤቱን ጓዳ፣ የእናቶችና የሕፃናትን ችግር የሚያውቁ፣ በቤት አያያዝና በህፃናት አስተዳደግ የተሻለ ክህሎትና ዘዴ ስላላቸው እንዲሁም አብዛኞቹ የጤና ችግሮች በእናቶችና ሕፃናት ላይ የሚከሰቱ በመሆናቸው ነው፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን አሰራር ከዚህ በፊት እንደተለመደው ተቋም ላይ በመመስረት አገልግሎትን ፈልጎ ወደ ጤና ድርጅት ሲመጣ ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን ሕብረተሰቡ በተለይም

እናቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ወደ ጤና ድርጅት ሳይመጡ በየቤታቸውና በየመንደራቸው በመሄድ ንቃተ ጤናንና የአገልግሎት ተጠቃሚነትን የሚያሳድግና በጤና ረገድ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት የሚያስችል አሠራርን ሁሉ ያካተተ ነው::

በመሆኑም ይህን ኘሮግራም በሀገር ደረጃ ወጥነት ባለው መልኩ ውጤታማ ለማድረግ የአፈፃፀም መመሪያ አሻሽሎ ማዘጋጀት አስፈልጓል:: መመሪያው እየሰራን በመማር፣ የተማርነውንና የተሻሉ ተሞክሮዎችን በማካተት ወደፊት የሚሻሻል ይሆናል:: ክልሎች ይህን መመሪያ መነሻ በማድረግ ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ በስራ ላይ እንዲያውሉት ይጠበቃል::

በዚህ መመሪያ የኘሮግራሙ ዓላማዎች፣ የአፈጻጸም ስልቶች፣ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ የአፈፃፀም ሂደት፣ የኘሮግራሙ ይዘት፣ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትና የመሳሰሉት ተካተዋል:: መመሪያው የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና በየደረጃው ያሉ የጤናና የመስተዳድር አካላት እንዲሁም ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲጠቀሙበት ታስቦ የተዘጋጀ ነው::

## 2. ትርጓሜ

### የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በፓኬጅ መልክ የተዘጋጀ፣ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ዋነኛ አካል ሲሆን ቤተሰብንና ማሕበረሰብን ማዕከል በማድረግ የሕብረተሰቡን ጤና ማሳደግ የሚያስችል እውቀትና ክህሎት በመፍጠርና አቅምን በማሳደግ ላይ የሚያተኩር፣ በሰለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚተገበር፣ በሽታን በመከላከል እና ጤናን በማጎልበት ሕብረተሰቡ የራሱን ጤና የሚወስነበትና እርምጃ የሚወስድበት የጤና አገልግሎት ድልድይ ነው::

## የቤተሰብ ፓኬጅ

የቤተሰብ ፓኬጅ ማለት በአንድ ቀበሌ ከሚገኘው ህብረተሰብ መካከል ቀዳሚ የለውጥ አራማጆች ሌሎች አርአያ የሚሆኑ አባወራዎችና እማወራዎችን በፈቃደኝነት በመምረጥ በሰለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አማካኝነት ስልጠና በመስጠትና ቤት ለቤት ድጋፋዊ ጉብኝት በማድረግ የጤና ፓኬጆችን እንዲተገብሩ በማድረግ ለሌሎች ምሳሌ በመሆን በሽታን መከላከልና ጤና የማበልጸግ ተግባራትን በመፈጸም ጤናን እንዲያመርቱና እንዲያባዙ የሚያስችል ስልት ነው::

## የማህበረሰብ ፓኬጅ

የማህበረሰብ ፓኬጅ ማለት በአንድ ቀበሌ የሚገኘውን የተለምዶ ማህበራት ማለትም ዕድር፣ዕቁብ፣የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የመንግሥት አወቃቀር ለምሳሌ ትምህርት ቤቶች የብዙኃን ማህበራትን ማለትም የሴቶች፣

የወጣቶች፣ የአርሶ አደር፣ ወዘተ ማህበራትን በመጠቀም እንዲሁም በውሎ ገብ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች፣ የቀበሌው ህብረተሰብ በአጠቃላይ በጤና ላይ ያለውን ግንዛቤ አዳብሮ በሽታ መከላከልን በባለቤትነት እንዲመራ እንዲሁም የአገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችል ስልት ነው::

## የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም መሠረታዊ ፍልስፍና

የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ፍልስፍና በሰለጠኑ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አማካኝነት የጤና መልዕክቶችንና ተግባራትን ወደ እያንዳንዱ ቤትና ቤተሰብ በማድረስ የሕብረተሰቡን ንቃተ ጤና በማሳደግ አዎንታዊ አመለካከት ማምጣትና እንደ ግብርና ምርት ሁሉ የጤና ምርት እንዲያመርት ማስቻል ነው::

## 3. የጤና ኤክስቴሽን ፕሮግራም ዓላማ

### 3.1. ዋና ዓላማ

የሕብረተሰቡን ጤና በማዳበርና በሽታን በመከላከል ተግባር ላይ ያተኮረ፣ ቤተሰብንና ሕብረተሰብን ማዕከል ያደረገ የጤና አገልግሎት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለሕዝቡ ማዳረስ ነው::

### 3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ሕብረተሰቡ የጤና አገልግሎቱን በቅርብ ወደ ሚያገኝበት አካባቢ በማደራጀት ህብረተሰቡ በራሱ የጤና ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠት እንዲችል ማስቻል

- የጤና ግንዛቤን በማሳደግ ጤናማ አስተሳሰብና ባሕሪ በመፍጠር፣ በህብረተሰቡ ዘንድ የጤና ክብካቤንና በሽታን የመከላከል ተግባራት ማጎልበት
- በእናቶችና ህፃናት ጤና ላይ የበለጠ ትኩረት በመስጠት የእናቶችንና የህፃናትን ጤናን ማበልፀግ
- መሰረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋንንና ጥራትን ማሳደግና ሕብረተሰብ መሠረት ያደረገ የጤና አገልግሎት የቅብብሎሽ ሥርዓት ማዳበር፣

## 4. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአፈጻጸም ስልቶች

- የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማጠናከርና ማጎልበት፣
- የልማት አጋር ድርጅቶችን ተሳትፎ ማጠናከርና የቅንጅት አሰራርን ማስፈን፣
- የተነሳሽነት፣የቁርጠኝነትና የተጠያቂነት አሰራርን ለማስፈን ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ ሠራተኞችን ለዚህ ፕሮግራም ተስማሚ አድርጎ ማዘጋጀት ፣
- በየደረጃው ተገቢውን የፖለቲካ ቁርጠኝነትና ድጋፍ ማጎልበት ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን በዘላቂነት መደገፍ የሚያስችል የግብአት አቅርቦት ሥርዓት ማጠናከር/ በሰው ኃይል፣ በቁሳቁስ፣ በገንዘብ፣ ወዘተ/ ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ድጋፍ የሚሰጡ የጤና ተቋማትንና ማሰልጠኛ ማዕከላትን ማጠናከር ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን የሙያ ብቃት የሚያጎለብቱ ተከታታይ ስልጠናዎች ማካሄድ ፣
- በውጤት ተኮር ላይ የተመሰረተ ሥርዓት ዘርጋት፣
- ሞዴል ቤተሰቦች በመምረጥ የማሸጋገሪያ ሥራ መሥራትና ወደ ሌሎች ቤተሰቦች ማስፋፋት ፣

- በቀበሌ የሚኖረውን የሁሉንም ህብረተሰብ ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማህበረሰብ አቀፍ አገልግሎት ማሳደግ፣
- የበጎ ፈቃደኛ የማህበረሰብ ጤና ማስፋፊያ እንቅስቃሴን ማጠናከር ፣
- ከጤና ጣቢያዎች ጋር ቅብብሎሽንና ትስስርን ማጠናከር
- ተቋማትን መጠቀም፣ ለምሳሌ ከትምህርት ቤቶችና ከአርሶ አደር ማሰልጠኛዎች ጋር አርአያ እንዲሆኑ በጋራ መሥራት ፣
- አሳታፊ የሆነ የድጋፋዊ ክትትልና የግምገማ ሥርዓትን ማጠናከር ፣
- የፕሮግራሙ አፈጻጸም በነፃ አጥኚ አካላት በየጊዜው እንዲገመገምና በተገኘው ውጤት መሰረት እንዲሻሻል ማድረግ ፣

## 5. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አደረጃጀት፣ የሥራ ተግባርና ኃላፊነት

ለጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ተግባራዊነት በየደረጃው አደረጃጀት መፍጠርና የሥራ ኃላፊነት መለየት አስፈላጊ በመሆኑ የወረዳ አስተዳድር ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠትና ተገቢውን የአሠራር ስልት በመቀየስ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል። የቀበሌ አስተዳድርም በፕሮግራሙ ላይ ከማቀድ ጀምሮ እስከ መተግበር ድረስ በባለቤትነት የመሳተፍ፣ የመደገፍ፣ የመከታተልና የመገምገም ኃላፊነት አለበት።

የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም በቀበሌ ደረጃ የሚሰጥ አገልግሎት ነው። በሀገሪቱ የጤና አገልግሎት እርከን የጤና ኬላ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የሚገኝና በቀበሌ

ደረጃ የሚዋቀር የጤና ተቋም ሲሆን በአማካይ 5,000 ሰዎችን እንዲያገለግል ሆኖ የተደራጀ ተቋም ነው:: በአንድ የጤና ኬላ ሁለት ሴት የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሚመደቡ ሲሆን ከሁለቱ አንደኛዋ የጤና ኬላ ኃላፊና የቀበሌ ካቢኔ አባል በመሆን ትሰራለች:: የጤና ኬላ ኃላፊዋን የመምረጡና የመመደቡ ተግባር በወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤትና በቀበሌው አስተዳድር በጋራ የሚከናወን ይሆናል:: የአካባቢው የሕብረተሰብ በጎ ፈቃድ ጤና ሠራተኞች ማለትም የቀበሌ ጤና ተጠሪዎች፣ የሰለጠኑ የልምድ አዋላጆች፣ የሥነ ተዋልዶ ጤና ተጠሪዎች ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተጠሪ በመሆን አጋዥ ሆነው ይሰራሉ::

"ሁሉም መንገዶች ወደ ጤና ኤክስቴንሽን ያመራሉ" በሚለው መርህ መሰረት ፕሮግራሙን፣ ለመምራት፣ ለማስተባበር፣ ለማስፈፀምና ለመከታተል ከፌዴራል እስከ ቀበሌ ድረስ መዋቅር በመዘርጋትና በየደረጃው የሚገኙ የሥራ ክፍሎችም ተግባርና ኃላፊነትን መወጣት ይጠበቅባቸዋል::

## 5.1 **የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት**

- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን የማጣቀሻ ጽሑፎችን፣ የሥራ መመሪያዎችንና ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ማምረትና ቁሳቁሶችን ማቅረብና ማሰራጨት እንዲሁም በዚህ ዙሪያ ለክልሎች ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት ፣
- ግብአትን ለማሟላት ከአጋር ድርጅቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራርንና ትብብርን ማጠናከር ፣
- የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ማዘጋጀት ፣

- ከፌዴራል መንግሥት፣ ከሴክተር የሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ከክልል ምክር ቤቶች፣ ከጤና ቢሮዎችና አግባብነት ካላቸው አጋር ድርጅቶች ጋር መረጃ መለዋወጥ ፣
- የፕሮግራሙን አፈጻጸም ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ማካሄድ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሥራ ላይ ሥልጠናና ቀጣይ ትምህርት የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ወጥነት ያላቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ፣ ሪፖርት ማቅረቢያ፣ የክትትልና የግምገማ ቅጾችን ማዘጋጀትና ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች አብረው የሚሰሩበትን መመሪያ ማውጣትና ድጋፍ ማድረግ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ሰልጣኞች ሀገራዊ የሆነ መነሻ የምልመላ መስፈርት ማዘጋጀት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን ሥልጠና መደገፍና ውጤቱን መከታተል፣
- የክትትልና የግምገማ ሥራዎችን ማከናወን፣ ማስተባበርና መምራት ፣

## 5.2 የክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ግንባር ቀደም አጀንዳ አድርጎ መንቀሳቀስ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠልጣኞችን አገራዊ በሆነው መነሻ መሠረት ምልመላ ማገዝና ማስተባበር ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም ላይ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ማስተባበርና መደገፍ ፣
- ድጋፋዊ ክትትልና የሥራ ግምገማ ማድረግ ፣

- ለዞን ጤና መምሪያዎችና ለወረዳ / ልዩ ወረዳ / ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣ማምረትና ማሰራጨት ፣
- የልምድ መለዋወጫ መድረኮችን ማዘጋጀት ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እና የበጐ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች አብሮ የሚሠሩበትን ሁኔታ መፍጠርና መደገፍ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አፈፃፀም ላይ ጥናቶችን ማካሄድና መደገፍ፣
- ፕሮግራሙን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መሠረታዊ የሆኑ ግብአቶች መኖራቸውን ማረጋገጥና ማሟላት፣
- በክልሉ ለሚካሄደው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚጠቅሙ የመረጃ ሥርዓቶችን ማጠናከርና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን ማዘጋጀት፣
- የህሙማን አላለክንና አቀባበልን በተመለከተ መመሪያ ማውጣት፣
- ወቅታዊ የሥራ ሪፖርቶችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና በማዘጋጀት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ማቅረብ፤ ለሌሎችም አጋር ድርጅቶች ማሳወቅ ፣

## 5.3 የዞን ጤና መምሪያ ተግባርና ኃላፊነት*

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ግንባር ቀደም አጀንዳ አድርጎ መንቀሳቀስ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠልጣኞችን ምልመላ ማገዝና ማስተባበር ፣

* የዞን ጤና መምሪያ መዋቅር በሌለባቸው ክልሎች በዞን ጤና መምሪያ ሥር የተዘረዘሩት ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በክልሉ ጤና ቢሮ ወይም በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች ሊከናወኑ ይችላሉ::

- በጤና ኤክስቴንሽን አፈጻጸም ላይ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ማስተባበርና መደገፍ ፣
- ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤቶች የቴክኒክና የአስተዳደር ድጋፍ መስጠት ፣
- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣ ማምረትና ማሰራጨት፣
- የልምድ መለዋወጫ መድረኮችን ማዘጋጀት ፣
- በዞኑ ለሚካሄደው የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚጠቀሙ የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችና የመረጃ አሰባሰብ ሥርዓቶችን ተግባራዊ ማድረግ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የግምገማ መድረኮች ማዘጋጀት ፣
- ከአጋር ድርጅቶች ጋር ሊኖር የሚገባውን ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር ማጎልበትና ማጠናከር ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ጋር በመመሪያው መሰረት መስራት እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- ለክልል ጤና ቢሮዎች በየወቅቱ ሪፖርት ማዘጋጀትና ማቅረብ፣

## 5.4. የወረዳ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ሠልጣኞችን ምልመላ መከታተል፣ ማገዝና ማስተባበር፣
- በየቀበሌው የጤና ኬላንና ለአምስት ጤና ኬላዎች አስኳል ጤና ጣቢያዎችን መገንባት
- ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አስፈላጊውን ግብአት (ገንዘብ፣ ቁሳቁስ፣ የሰው ኃይል፣ ወዘተ.) መመደብና ማፈላለግ፣
- ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ግምገማ ማካሄድ ፣
- ለቀበሌ አስተዳደሮች ስለ ፕሮግራሙ አፈጻጸም አስፈላጊውን የሥራ መመሪያና ድጋፍ መስጠት፣

- መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በፕሮግራሙ ዙሪያ አስፈላጊውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ በማስተባበር ቅንጅታዊ አሰራርን ማስፈን፣
- በፕሮግራሙ ዙሪያ የሕዝቡን ተሳትፎና ንቅናቄ ማሳደግ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በታለመለት አቅጣጫ ለታለመለት ዓላማ በወረዳው ውስጥ መፈጸሙን ማረጋገጥ ፣

## 5.5. የወረዳ /የልዩ ወረዳ/ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ቁልፍ ተግባር አድርጎ መንቀሳቀስ፣
- የጤና ኤክስቴሽን ስራዎችን በቤተሰብና በሕብረተሰብ ደረጃ ማስተባበር፣ ተግባራዊ ማድረግ፣ መከታተል፣ መገምገም፣
- ድጋፋዊ የመስክ ክትትልና የሥራ ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረ መልስ መስጠት ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሥራ ላይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠናዎች ማዘጋጀትና መስጠት፣
- ለፕሮግራሙ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የጤና አገልግሎት ግብአቶችን፣ ቅጾችን፣ መመሪያዎችን፣ ፎርሞችን፣ ወዘተ. ማሟላት፣
- ከተለያዩ የሥራ ዘርፎችና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን መቅጠርና መመደብ ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ሰልጣኞች ምልመላ ወቅት ለቀበሌዎች ድጋፍ ማድረግ ፣

- ሕብረተሰቡንና አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር የጤና ኬላ ግንባታን ማስፋፋት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ጋር በመመሪያው መሰረት መስራት እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- በወረዳው ውስጥ በኤክስቴንሽን ፐሮግራምና ባሉት የጤና ተቋማት የህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓትን /Referral System / በማጠናከር ለጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አፈፃፀም አጋዥና አመቺ ማድረግ ፣
- የሥራ ሪፖርቶችን ማሰባሰብና ማጠናቀር፣ በየወቅቱ ለክልል ጤና ቢሮ/ ለዞን ጤና መምሪያ እንዲሁም ለወረዳ መስተዳድር ማቅረብ ፣
- አዳዲስ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ወደ ተመደቡበት ቀበሌ ሄደው ሥራ ከመጀመራቸው በፊት በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ከወረዳው አስተዳደር አካል ጋር በመሆን ወደ ተመደቡበት ቀበሌ በመውሰድ ከሕብረተሰቡ ጋር የትውውቅ ኘሮግራም ማካሄድ፣
- እንደወረዳው የጤና ተጨባጭ ሁኔታ ትኩረት የሚሠጣቸውን የጤና ጉዳዮች ጨምሮ አዲስ ተመራቂዎችን ወደ ሥራ ከመሠማራታቸው በፊት ሊኖራቸው የሚገባ የሥራ እንቅስቃሴ፣ የመረጃ አያያዝ፣ የሪፖርት አደራረግና ከሕብረተሰብና ከበጎ ፈቃድ የጤና ሠራተኞች ጋር እንዴት መሥራት እንደሚገባቸው ሥልጠና መስጠት፣

## 5.6 የጤና ጣቢያ ወይም የአስኳል/አዳጊ/ ጤና ጣቢያ ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በመስክ ልምምድ ተገቢ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዕቅድ፣ አፈጻጸምና ድጋፋዊ ክትትል ቁጥጥር ተግባራት ላይ መሳተፍ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሥራ ላይ የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና ላይ መሳተፍ፣
- የህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓትን መሠረት በማድረግ መተግበርና ተገቢውን ግብረመልስ ለጤና ኬላዎች መስጠት ፣
- ለጤና ኬላ የሚያስፈልግ የግብአት አቅርቦት ላይ የድርሻቸውን መወጣት ፣
- ከጤና ኬላዎች ጋር ተገቢውን የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ፣
- ለጤና ኬላዎች የቅርብ ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- ጤና ኬላዎችን ወይም የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችን በውሎ ገብ ሥራዎች ማገዝ፣

## 5.7 የቀበሌ አስተዳድር ተግባርና ኃላፊነት

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ሥራዎችን ማቀድ፣ ተግባራዊ ማድረግ፣ መቆጣጠር፣ መከታተል፣ መገምገምና ማስተባበር ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ የህብረተሰቡን አባላትና በቀበሌ ውስጥ ያሉ ሕዝባዊ፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማስተባበር፣መቀስቀስና ማንቀሳቀስ እንዲሁም በመካከላቸው ቅንጅታዊ አሠራርን ማስፈን ፣

- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በማሟላት በኩል እገዛ ማድረግ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና በበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ምልመላ ላይ መሳተፍ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የበጎ ፈቃድ የ ሕብረተሰብ የጤና ሠራተኞች አብሮ ተጋግዘው መሥራታቸውን ማረጋገጥ፣
- በጤና ኬላዎች ግንባታና እንክብካቤ ህዝብን በማስተባበርና አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማሟላት ተገቢውን እገዛ ማድረግ ፣

## 5.8. የጤና ኬላ /የጤና ኤክስቴሽን ሠራተኛ ተግባርና ኃላፊነት

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ተጠሪነታቸው ለቀበሌው አስተዳድርና ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

### 5.8.1. የአስተዳደር ተግባራት

- በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ መሰረታዊ የዲሞግራፊና የጤና ነክ መረጃዎችን መሰብሰብና መዝግቦ መያዝ፣
- ከቀበሌ አስተዳድርና ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ፕሮግራሙን ማቀድ፣ መምራትና ማስተባበር፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ተግባራት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ሟሟላትና ማስተዳደር፣
- የህሙማን አላላክና አቀባበል ሥርዓትን ማጠናከርና ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመረጃ ማጠናቀሪያ መዝገቦችና ሰነዶች መኖራቸውን ማረጋገጥና መጠቀም ፣

- የዶክሜንቴሽን ሥርዓትን መዘርጋትና የፋይል አያያዝን ማጠናከር ፣
- የቀበሌውን የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ዕቅድ ከሕብረተሰብና ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ የጤና ሠራተኞች ጋር በመተባበር ማዘጋጀት፣
- የሚያስፈልጉ መድኃኒቶችንና የሕክምና መገልገያዎችን በወቅቱ መጠየቅ፣ ሲፈቀድም መረከብና በመንግስት የንብረት አያያዝ ገቢና ወጪ በማድረግ በትክክል መጠቀም ፣
- መድኃኒቶችና የሕክምና መገልገያዎች ብልሽት እንዳይደርስባቸው በአግባቡ መያዝ፣ ጊዜ ያለፈባቸውና የማይፈለጉ ሲኖሩ ለወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ማሳወቅ ፣
- በየወቅቱ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቀበሌ ምክር ቤት፣ ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤትና ለጤና ጣቢያ መላክ፣

## 5.8.2. ጤናን የማዳበርና በሽታን የመከላከል ተግባራት

- የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞችን ማደራጀት፣ማሰልጠንና ማስተባበር፣
- በመደበኛነት የቤት ለቤት ጉብኝት ማድረግ ፣
- የጤና አገልግሎት ያቋረጡትን መለየትና እንዲቀጥሉ ማድረግ ፣
- በቀበሌው ውስጥ ልዩ ልዩ የጤና ማበልፀግና በሽታን የመከላከል /የክትባት አገልግሎት፣ የቤተሰብ እቅድ፣ የጤና አጠባበቅ ትምህርት፣ የሥነ ምግብ ትምህርት፣ የተጨማሪ ምግብ፣ የታመመ ህጻን አመጋገብ፣ የእድገት ክትትል፣የስነምግብ ልየታ፣ የነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች አመጋገብ፣ የማይክሮኑትሬት እደላ፣ የቅድመ ወሊድ የጤና ክብካቤ፣ የማዋለድ አገልግሎት፣ የድህረ ወሊድ የጤና ክብካቤ፣ የተቀናጀ የህጻናት ህክምና

አገልግሎት፣ የጨቅላ ህጻን ክብካቤ፣ የወጣቶች ስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት፣ የበሽታዎች አሰሳ ጥናት፣ የግል ንፅህና አጠባበቅ፣የሽንትና የአይነ ምድር አወጋገድ፣ የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ፣ የውኃ አቅርቦትና ንጽሕና አጠባበቅ፣ የምግብ ንጽሕና አጠባበቅ፣ የመኖሪያ ቤት ንጽህና፣ የተባይና የቆርጣሚ እንስሳት ቁጥጥር፣ የቲቢና የወባ በሽታ መከላከልና መቆጣጠር፣ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስና በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች መከላከልና መቆጣጠር/ ተግባራትን ማከናወን፣

- የሕብረተሰቡ አባላት የጤና አራማጆች እንዲሆኑ ሥልጠና መስጠት ፣
- የጤና አገልግሎትን በማስመልከት ሕብረተሰቡን መቀስቀስና በዘመቻ ማንቀሳቀስ፣
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን ፖሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫዎች፣ የጤናውን ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር ማወቅና መተግበር ፣

### 5.8.3. የመጀመሪያ ደረጃ የህክምናና የሪፈራል አገልግሎትን መስጠት

በማህበረሰብ የጤና አጠባበቅ ሥራ ማከምና መከላከል ተነጣጥለው ወይም ተለያይተው የሚሄዱ አይደሉም:: ህብረተሰቡ በአገልግሎቱ እንዲያምንና በሙሉ ልብ እንዲተባበር ህዝቡ ከሚፈልገውና ከሚያውቀው መነሳት ተገቢ ነው::

ከህመም የሚፈውስ መድኃኒት ለህመምና ስቃይ የመጀመሪያ ምላሽ ነው:: ሰዎች ቢያንስ መጀመሪያ ይህን ፈውስ ይፈልጋሉ:: ለፈውስ ምክር በመለገስ በመከላከሉ ሥራ የህብረተሰቡን አመኔታ ማግኘት ይቻላል:: ያልዘገየ፣ አስተማማኝና በቀላል ወጪ በቤታቸው የሚሰጥ ቀላልና አስፈላጊ የህክምና እርዳታና ምክር የመከላከል ሥራ አካል

ነው። በመሆኑም የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሕብረተሰቡ ለሚፈልገው ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

ስለሆነም በአብዛኛው ዋና የጤና ችግር ለሆኑ ህመሞች ለምሳሌ ወባ፣ ተቅማጥ፣ የሆድ ትላትል፣ ትራኮማና እከክ ለመሳሰሉት ህክምና መስጠት ይኖርባቸዋል። ከዚህ በመነሳት ስለመከላከል ማስተማር፣ ማስረጽና ማሳመን ያስፈልጋል። ከአቅማቸው በላይ ሲሆን ደግሞ ሕመምተኞችን በአቅራቢያው ወደሚገኝ ጤና ጣቢያ መላክ ይኖርባቸዋል።

### 5.8.4. የተለያዩ የመግባቢያ/የኮሚኒኬሽን ዘዴዎችንና ክህሎትን መጠቀም

ከላይ የተዘረዘሩትን ተግባራትና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት የኮሚኒኬሽን ወይም የመግባቢያ ዘዴ ዕውቀትና ክህሎት መታጠቅ አስፈላጊ ነው።

ኮሚኒኬሽን ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች ሐሳብ ተለዋውጠው መግባባት ላይ የሚደርሱበት መድረክ ነው። ከተግባቡ በሐሳብ አንድ ይሆናሉ ወይም ይተማመናሉ ማለት ነው። ከተማመኑ ውጤት አለ፤ ውጤት ደግሞ ለውጥ ያመጣል።

በፓኬጆች የተካተቱ እውነታዎችና ሳይንሳዊ ይዘት ያላቸው ጥልቅ ሐሳቦችን ብቻ ይዞ ወደ ሕብረተሰብ በመግባት ለውጥ ማምጣት ይከብዳል። ስለሆነም ሐሳቦቹ በኮሚኒኬሽን ክህሎትና ጥበብ ሊታገዙ ይገባል። የሚተላለፉ መልዕክቶችም፣

- ግልጽ፣ አጭርና ቀላል ለመተግበር ብዙ ጊዜ፣ ጉልበት ወይም ገንዘብ የማይጠይቁ ፣

- ጠቀሜታን የሚያጎሉ፣ ሰዎች ለምን ይህንን ተግባር እንደሚፈፅሙና ምን ጥቅም እንደሚያገኙ የሚያሳውቁ ፣
- የሚታመኑና ተግባርን በመፈፀም ሊመጣ የሚችለውን ጥቅምና ለውጥ አጉልተው የሚያሳዩ፣
- አዝናኝና ሳቢ ለማድረግ የተለያዩ የመልዕክት ማስተላለፊያ ዘዴዎችን የያዙ ፣
- ለድርጊት የሚገፋፉ፤ ማን ምን ማድረግ እንዳለበት፣ መቼ፣ የትና እንዴት መከናወን እንዳለባቸው የሚገልጹ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

መልዕክቶችን በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም ሰው በሰው፣ በድራማ፣ በጭውውት፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ በሥነ-ቃል፣ በዘፈን፣ በግጥም፣ ካርድ ሰርቶ በማሳየት፣ ወዘተ. ለማህበረሰቡ ማስተላለፍ መለመድ አለበት፡፡

## 5.9. የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት

- አርአያ መሆንና ሌሎች የለውጥ አራማጆችን ማፍራት ፣
- ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አጋዥ በመሆን በጋራ ማቀድ፣ መተግበርና የጤና ሥራዎችን ክትትል ማድረግ ፣
- በተለያየ ጊዜና ቦታ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት፣
- በጤና አጠባበቅ ዙሪያ ሕብረተሰቡን ማስተባበርና መቀስቀስ ፣
- በአካባቢው ወረርሽኝና አዲስ በሽታ ሲከሰት በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ፣
- የጤና አገልግሎት ያቋረጡትን መለየትና እንዲቀጥሉ ማድረግ ፣

- የታቀዱ የቤተሰብና የሕብረተሰብ ጤና አገልግሎቶች በበጐ ፈቃደኝነት በያዟቸው ቤተሰቦች ዘንድ መድረሱንና መፈፀሙን ማረጋገጥ
- በቀበሌ የጤና መረጃ አሰባሰብ ላይ መሳተፍ ፣
- የተከናወኑ ተግባራትን በየጊዜው ለጤና ኬላ ወይም ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ሪፖርት ማድረግ ፣
- የሞዴል ቤተሰቦች ቁጥር እንዲባዙ በሞዴል ቤተሰብ የሚተገበሩ ፓኬጆችን ማስረዳትና ማሳየት፣

5.10. **የሞዴል ቤተሰብ ተግባርና ኃላፊነት**

- በቤተሰብ አቀፍ የጤና ፓኬጅ እቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸምና ግምገማ ላይ መሳተፍ ፣
- በቁርጠኝነት ስልጠናውን ማጠናቀቅ፣ በስልጠ ናውም መሰረት መተግበር፣
- በአካባቢው ወረርሽኝና አዲስ በሽታ ሲከሰት በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ፣
- በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀምና የፈ ጠራ ችሎታን በማከል የቤተሰብ አቀፍ ፓኬጅን ተግባራዊ ማድረግ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ስራ ከሞዴልነት አልፎ ወደ ሌሎች አካባቢዎች እየተስፋፋ በቀጣይነት እንዲሄድ ሕብረተሰቡን በአርአያነት ማስተማር፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ሥራ የተሳካ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ፣

5.11 **የሕብረተሰቡ ተግባርና ኃላፊነት**

- በቀበሌው የጤና ዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸምና ግምገማ ላይ መሳተፍ ፣
- የተሰጠውን የጤና አጠባበቅ ትምህርት በተግባር መተርጐም ፣
- በአካባቢው ወረርሽኝና አዲስ በሽታ ሲከሰት በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ፣
- በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመጠቀምና የፈ ጠራ ችሎታን በማከል የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ተግባራዊ ማድረግ ፣
- በተለያዩ ማሕበራት ተደራጅተው የአካባቢያቸውን የጤና ችግሮች መፍታት፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ሥራ የተሳካ እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ ፣
- በተለያዩ የጤና ንቅናቄ ሥራዎች ላይ መሳተፍ፣
- በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት ግንባታና የጤና ክብካቤ ሥራዎች ላይ መሳተፍ፣

5.12. **የትምህርት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት**

ትምህርት ቤቶች ሀገሪቱን የሚተካና ከመሃይምነት የተላቀቀ ዜጋ የሚያፈሩ እንደመሆናቸው መጠን ጤናን ሊያዳብሩ በሚችሉ ተግባራት ላይ በንቃት መሰማራት ይጠበቅባቸዋል::

የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በየቀበሌው ከመተግበር አኳያ የመምህራንና የተማሪዎች ሚና በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ተማሪው ከእያንዳንዱ ቤተሰብ የወጣ እንደመሆኑ መጠን የጤና መልዕክቶችንና ጭብጥ ተግባራትን ወደ እያንዳንዱ ቤት ለማዳረስ ትልቅ እገዛ አለው:: ከዚህም በላይ ጤናማ ትውልድ በመተካት የሀገሪቱ

የጤና ሁኔታ አሁን ካለበት ደረጃ የተሻለ እንዲሆን አስተዋጽኦው ከፍተኛ ነው፡፡

ይህንኑ እውን ለማድረግ በተለይም የሐይጂንና የሳኒቴሽን ሥራዎችን በት/ቤቶች ለማስፋፋት የትምህርት ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒሰቴርና የውሃ ሀብት ሚኒስቴር የጋራ ስምምነት ተፈራርመዋል፡፡ ስለዚህ ይህን አመቺ ሁኔታ በመጠቀም የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራምን በሕብረተሰቡ ለማስፋፋት መምህራንና ተማሪዎች ሊሰጡ የሚችሉትን ድጋፍ ሥርዓት ባለው መንገድ ለማራመድ የሚያስችል አሠራር መቀየሱ ተገቢ ነው፡፡ ስለሆነም፣

- የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ አንድ ኘሮግራም እንዲተገበር ለማስቻል በኘሮግራሙ ዙሪያ ሁሉም መምህራን እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- ተማሪዎች ማደራጀትና ስልጠና መስጠት ወይም የትምህርት ቤት የተለያዩ ክለቦች መጠቀም፣
- ኘሮግራሙን በቤታቸው ለመተግበር ፈቃደኛ የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት በመምህራን መሪነት በቡድን ማደራጀት፣
- የጤና ፖኬጁን በትምህርት ቤቶች በሞዴልነት መተግበርና ተማሪዎችን ማስተማር
- ዕድሜያቸው ለአቅመ ሄዋን የደረሱ ሴት ተማሪዎች የክትባት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ፣
- የተማሪዎችን የግል ንጽህና መቆጣጠር፣
- የተለያዩ የጤና ተግባራትን የሚያመለክቱ ሰርቶ ማሳያዎችን በት/ቤት በማዘጋጀት /መጸዳጃ ቤት፣ የእጅ መታጠቢያ፣ የቆሻሻ ጉድጓድ፣ ወዘተ./ እንዲጠ ቀሙ በማድረግ የተማሪዎችን እውቀትና ክህሎት ማሳደግ

- ተማሪዎች በት/ቤት የቀሰሙትን የጤና ትምህርት በየቤተሰቦቻቸው እንዲያስፋፉ ማስቻል፣
- መደበኛውን ትምህርት ሂደት በማያስተጓጉል ሁኔታ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች በሳምንት የተወሰነ ሰዓት በትምህርት ቤት ስለጤና አጠባበቅ ትምህርት የሚሰጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፣

## 5.13. የቡዙኃን ማሕበራት ተግባርና ኃላፊነት

በቀበሌ ደረጃ የተደራጁ የሴቶችና የወጣት ማሕበራት እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ማሕበራት በጤና አጠባበቅና በጤና አገልግሎት የመጀመሪያ ተደራሲ የሆነውን ማሕበረሰብ የሚያቀፉ ናቸው፡፡ በመሆኑም በየማህበራቱ ለጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ውጤት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለሆነም፣

- የማሕበራት አመራሮች እራሳቸውን ግንባር ቀደም እና ሞዴል ማድረግ፣
- ሌሎች አባላትን በጤና አጠባበቅ ተግባራት እንዲሳተፉ ማበረታታት፣
- ሴቶችንና ወጣቶችን በጤና ጉዳይ በማሕበረሰብ ውይይት ማሳተፍ፣
- ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በመወያየት የአገልግሎት አሰጣጡን እንዲሻሻል መጣር፣
- በዕቅድ አተገባበርና ግምገማ ላይ መሳተፍ፣
- በጤና ኬላ ግንባታና ጥበቃ ላይ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ፣
- ከሌሎች የማሕበረሰብ የተለምዶ ማሕበራት ማለትም የዕድር፣ የዕቁብ፣ የሃይማኖት፣ የጽዋ፣

ወዘተ. መሪዎች ጋር በመመካከር ሰፊ
የማሕብረሰብ ንቅናቄ ለመፍጠር የበኩላቸውን
ድርሻ መወጣት፣

## 5.14. **የአጋር ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት**

- ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችና በነሱም በኩል ለበጎ ፈቃደኛ የሕብረተሰብ የጤና ሠራተኞች የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን አጀንዳቸው አድርገው መንቀሳቀስ ፣
- በቀበሌው ውስጥ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በመጠቀም የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት ፣

# 6. በቀበሌ ደረጃ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የአተገባበር ሂደት

## 6.1 መርሆዎችን መከተልና በጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም ላይ ስምምነት መድረስ

### 6.1.1. የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሊከተሏቸው የሚገቡ መርሆዎች

- የሕብረተሰቡን አኗኗር፣ ባህላዊ ልምዶችና እምነቶችን ማወቅና ማክበር ፣
- በማንኛውም ጊዜና ቦታ ከሕብረተሰቡ አባላት ጋር ሲገናኙ በባህሉ መሰረት ሰላምታ መለዋወጥና ማሕበራዊ ግንኙነትን ማጠናከር፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ላይ የሚከናወኑ ተግባራትን ዓላማ ለሕብረተሰቡ ግልጽ ማድረግ፣ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማጎልበት ፣
- የሕብረተሰቡን ዕውቀት፣ ክህሎትና ዘዴዎች መጠቀም ፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ላይ ሕብረተሰቡ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ማድረግ ፣
- ከቀበሌ ነዋሪዎች ጋር መገናኘት ሲያስፈልግ ሕዝቡ በሚመቸው ሰዓትና ቦታ እንዲሆን ማድረግ፣
- በውይይት ጊዜ የሚሰጠውን ማሳሰቢያ፣ አስተያየትና ማበረታቻ በአክብሮት መቀበልና ማመስገን ፣
- እየሰሩ መማር፣
- የመልካም ስነ ምግባር ባለቤት መሆን ፣
- ሕብረተሰቡን ማዳመጥ መማርና አብሮ መሥራት ፣
- ችግሮችን ደረጃ በደረጃ መፍታት መልመድ፣

- የኮሚኒኬሽን ክህሎትን ማሳደግ፣
- በፕሮግራሙ አፈጻጸም ዙሪያ የተገኙትን ተመክሮዎችና ዘዴዎች ማስፋፋት፣
- በፕሮግራሙ አፈጻጸም ዙሪያ ውጤት በማምጣት ላይ ማተኮር ፣

**6.1.2. ስለ ፕሮግራሙ ግንዛቤ ማስጨበጥና ስምምነት ላይ መድረስ**

- ከቀበሌው መስተዳድር ጋር በመወያየት አፈጻጸሙን ለመከታተል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት መፍጠር ፣
- በቀበሌው ታዋቂ ግለሰቦችና ተደማጭነት ያላቸው ሰዎች በመለየት በፕሮግራሙ አፈጻጸም ላይ ማወያየትና የጋራ ውሳኔ ላይ መድረስ ፣
- በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ የሚታቀፉትን የሕብረተሰብ አበላት በመለየት ስምምነት ላይ መድረስ፣
- ተከታታይ የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠ ትና ለለውጥ ማነሳሳት ፣

6.1.3. **መረጃ ማሰባሰብና ማቀድ**

- በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙትን ሕዝባዊ ማሕበራት /የወጣቶች ማህበር፣የሴቶች ማህበር፣የአርሶ አደሮች ማህበር፣ እድር፣ ዕቁብ፣ ወዘተ./ እንዲሁም ተሰሚነትና የሥራ ቅርበት ያላቸው አካሎች መለየትና በመረጃ አሰባሰብ ሂደት መጠቀም፣
- ስለቀበሌው የጤና ገጽታ (Health Profile) ማዘጋጀት፣ /በቀበሌው ውስጥ የጤና ተቋማት፣

የውሃ አቅርቦት፣ የሳኒቴሽንን አገልግሎት፣የጤና የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን፣ የመኖሪያን ቤቶችን፣ ወዘተ./ በሚያሳይ መልኩ የቀበሌውን ካርታ ማዘጋጀት፣

- በቀበሌው በሞዴል ቤተሰብ ለማቀፍ የመነሻ ጥናት (Baseline survey) መስራትና ማዘጋጀት፣
- በጤና ኤክስቴንሽን ፓኬጅ በሞዴልነት የሚታቀፉትን ቤተሰቦች መለየትና ቁጥራቸው በአንድ ጊዜ ከ40-60 የሚሆኑ ቤተሰቦችን በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ማቀፍ፣ ሌላውን የሕብረተሰብ ክፍል ደግሞ በሕብረተሰብ አቀፍ ፓኬጅ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል፣
- የልደት፣የጋብቻ፣ የፍልሰትና የሞት መረጃዎችን በማሰባሰብ ለዕቅድ ሥራ ማዋል፣

## 6.2 የሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ የትግበራ ሂደት

### 6.2.1 ሥልጠና

በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ አጀማመር ወቅት ቅድሚያ የቤተሰብ መረጣ ከዚያም ከተመረጠው ቤተሰብ ጋር ስምምነት ላይ መድረስ ያስፈልጋል፡፡ በትግበራ ሂደት ደግሞ ለሞዴል ቤተሰቦች ተከታታይ ስልጠና መስጠት የግድ ነው፡፡ ከስልጠና እስከ ምረቃ ድረስ ያለው ሂደት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- ለመጀመሪያ ጊዜ በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ አገልግሎት ታቅፈው ሥልጠናውን የሚወስዱ ቤተሰቦች ትምህርቱን ቶሎ የሚቀበሉ፣ ታታሪ፣ አርአያ፣ ለለውጥ ዝግጁ እና ፈቃደኛ የሆኑ፣
- በማንኛውም የልማት ሥራ ጉልህ ሚና የነበራቸውና ሌሎችን ለማሳመንና ለመቀየር ፍላጎት እና ብቃት ያላቸው ፣

- በግብርና ኤክስቴንሽን የታቀፉ ቤተሰቦች፣ የልምድ አዋላጆች፣ የቀበሌ ጤና ተጠሪዎችና ሌሎች የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች በመጀመሪያው ዙር ቢታቀፉ ይመረጣል፡፡ እነዚህ ቀዳሚ የለውጥ አራማጆች ለሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች አርአያ ስለሚሆኑ ለውጡን ለሕብረተሰቡ ለማዳረስ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል፡፡
- ስልጠናው በየንዑስ ቀበሌው ወይም በሞዴል ለታቀፉት ቤተሰቦች አማካይ በሆነ ቦታ መካሄድ አለበት፡፡
- በአንድ ጊዜ ማሰልጠን የሚቻለው ከ40-60 ቤተሰቦችን ሲሆን በዚሁ አሰራር ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ ማሰልጠን ይቻላል፡፡
- ስልጠናው በቀን እስከ ሁለት ሰዓት ሕብረተሰቡ በሚመርጠውና በሚመቸው ጊዜና ቦታ በጋራ ተወስኖ፣ እቅድ ወጥቶለት የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶ መሰጠት አለበት፡፡
- ሥልጠናው ሲሰጥ የተለያዩ ዘዴዎች ለምሳሌ የማሕበረሰብ ውይይት፣ ሰርቶ ማሳያ፣ የልምድ ልውውጥ፣ ጥያቄና መልስ፣ የቡድን ውይይቶችና ሌሎችም ዘዴዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡
- 75% የሚሆነውን የስልጠና ጊዜ የተከታተሉና የተገበሩ ቤተሰቦች እንዲበረታቱ ለምረቃ ብቁ ይሆናሉ፡፡
- በምረቃ ጊዜ የተማሩትን ለመተግበር ቃል ይገባሉ፡፡
- በምረቃ ጊዜም ከአጐራባች ጐጦች የተውጣጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች እንዲገኙ ማድረግ ለቀጣይ የማስፋፋት ሂደት ይጠቅማል፡፡

## በሥልጠናው ላይ የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች

| ርዕስ | ሰዓት | የማስተማሪያ ዘዴ |
|---|---|---|
| 1.**መሠረታዊ የሐይጂንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ**<br>• የግል ንሕጽና አጠባበቅ<br>• የውሃ ንጽሕና አያያዝና አጠቃቀም<br>• የምግብ ንጽሕና አጠባበቅ<br>• የመጸዳጃ ቤት አሠራርና አጠቃቀም<br>• የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ<br>• የመኖሪያ ቤት አሠራርና አያያዝ<br>• የተባዮችና የቆርጣሚ እንስሳት ቁጥጥር | 30 | ቲዎሪና ሠርቶ ማሳያ |
| 2. **የቤተሰብ ጤና ክብካቤ**<br>• የእናቶችና የሕፃናት ጤና ክብካቤ<br>• የቅድመ ወሊድ አገልግሎት<br>• ጤናማ የወሊድ አገልግሎት<br>• የድህረ ወሊድ አገልግሎት<br>• የጨቅላ ሕፃናት ክብካቤ<br>• በቤት ውስጥ የታመመ ሕፃን ክብካቤ/አያያዝና ለህክምና ወደ ጤና ተቋም መውሰድ<br>• ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች<br>• የቤተሰብ ዕቅድ<br>• የክትባት አገልግሎት<br>• ሥነ ምግብና አስፈላጊ ንጥረ ምግቦች ማለትም ቫይታሚን ኤ ፣ አዮዲን፣ ብረትና የመሳሰሉት አስፈላጊነት<br>• የተመጣጠነ ምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ<br>• የእናት ጡትና የተጨማሪ ምግብ አስፈላጊነት<br>• የፀሐይ ብርሃን አስፈላጊነት<br>• የተቅማጥ በሽታን የመከላከል ዘዴ | 42 | ቲዎሪና ሠርቶ ማሳያ |
| 3. **የበሽታዎች መከላከልና ቁጥጥር፣**<br>• ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል፣ ለሕሙማንና ለወላጅ አልባ ህፃናት ድጋፍ ማድረግ<br>• የወባ መከላከልና ቁጥጥር<br>• የአጎበር አጠቃቀም<br>• የወባ ትንኝ መራቢያ ቦታዎች ቁጥጥር<br>• የወባ ወረርሽኝ ሲቀሰቀስ ለይቶ ማወቅ፣ መከላከልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ<br>• የቲቢ መከላልና ቁጥጥር<br>• የሕሙማን ክትትል<br>• የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ | 24 | ቲዎሪና ሠርቶ ማሳያ |

### 6.2.2 **የቤት ለቤት ጉብኝት**

ከስልጠና በኋላ ተከታታይ የቤት ለቤት ጉብኝት በማድረግ ማስተማር፣ ማግባባት፣ መደራደር፣ ማሳመን፣ ሰርቶ ማሳየትና ማበረታታት በቤተሰብ ደረጃ ለውጥ እንዲመጣ ያስችላል፡፡ አተገባበሩም በሂደት ወደ ሌሎች ጐረቤቶች፣ ጓደኞችና አጠቃላይ ሕብረተሰቡ እንዲሠርጽ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም ማሕበረሰቡን በኑሮ ዘዴ፣ በአመጋገብ፣ በጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆንና በአኗናር ለውጥ እንዲያመጣ ያስችላል፡፡ ስለሆነም ከልማት ሠራተኞችና ከመምህራን ጋር በመተባበር የተቀናጀ ሥራ መስራት ያስፈልጋል፡፡

አንድ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ በየቀኑ በአማካይ ከስድስት እስከ ስምንት ቤቶች በመጐብኘት ትምህርት ትሰጣለች፣ ሰርቶ ማሳያም ትሰራለች፡፡ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ አንዱን ሞዴል ቤተሰብ ቢያንስ ስምንት ጊዜ ያህል በመጎብኘት መሠረታዊ የሆኑ የጤና ሥራዎች ታከናውናለች፡፡

በአፈፃፀም ጊዜ በመጀመሪያ ሊተገበር የሚገባው የፓኬጅ ሥራ ቀላል ወጪ የሚጠይቅ፣ ለመስራትም ቀላል የሆነና ከሕብረተሰቡ አጠቃላይ አስተሳሰብና ስነ ልቦና ጋር የማይጋጭ መሆን አለበት፡፡ የመጀመሪያዎቹ ስራዎች ስኬታማ መሆን በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል መተማመንንና ጥሩ ትስስርን ስለሚፈጥሩ ለቀጣዩ ስራ ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ ስለዚህ ከግልና አካባቢ ንፅህና አጠ ባበቅና የቤተሰብ እንክብካቤ ጋር የተያያዙ ስራዎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ቢሰሩ ይመረጣል፡፡

**በመጀመሪያው ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች**

- የግል ንፅህና አጠባበቅ
- የመጸዳጃ ቤት አሠራርና አጠቃቀም
- የንፁህ ውሃ አያያዝና አጠቃቀም
- የእርግዝና ክትትል፣ የወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት
- የክትባት አገልግሎት
- የእናት ጡት ወተትና የአመጋገብ ሥርዓት
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት
- የነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች አመጋገብ ሥርዓት
- የጨቅላ ሕፃን ክብካቤ
- ወባን መከላከልና መቆጣጠር/የአጐበር አጠቃቀም፣ የትንኝ መራቢያ ቦታዎች ቁጥጥር፣ ወዘተ...
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር

**በሁለተኛ ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች**

- የምግብና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ
- የቤት ንፅህናና የቆሻሻ ማስወገድ ሥራ
- የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻዎች አያያዝና የአወጋገድ ዘዴ
- በራሪ ተባዮችንና ተናዳፊ ነፍሳትን መከላከልና መቆጣጠር
- የተመጣጠነ ምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ
- ለሕፃን ተጨማሪ ምግብ አስፈላጊነት
- የታመመ ሕፃን በቤት ውስጥ ማከምና ወደ ጤና ድርጅት ስለመውሰድ
- የወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤናና ቅድመ ጋብቻ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራ
- ቲቢ መካከልና መቆጣጣር
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ
- ወረርሽኞችን ማወቅ፣ መከላከልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ

**በሶስተኛ ምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች**

ባለፉት ወራት የተገኙ ልምዶችን፣ የሕብረተሰቡ የእውቀትና የአስተሳሰብ ደረጃ እያደገ ሲሄድ በሕብረተሰቡ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሰርፀው የቆዩ ጎጂ ልማዶች መቀየር አለባቸው:: መቀየር የሚገባቸው ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችም የሚከተሉት ናቸው::

- የሴት ልጅ ግርዛት
- እንጥል መቁረጥ
- ጥርስና ድድን መቧጠጥ
- ዋግምት
- ያለዕድሜ ጋብቻ

ማሳሰቢያ:- የተግባራት የአፈፃፀም ምዕራፍ እንደ ፍላጐት፣ ምርጫ፣ የሥራው ክብደትና ቅለት፣ ወጪ እንዲሁም ልምድ ጋር ተያይዞ የሚፈጸም በመሆኑ ቤተሰቡ ከሚፈልገውና ከሚመቸው በመጀመር ሁሉንም ተግባራት ደረጃ በደረጃ መፈጸም ይጠበቅበታል::

### 6.2.3. **የጤና ኤክስቴንሽን ሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ማስፋፋት**

የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራምን በሞዴል ቤተሰብ ፖኬጅ ለማስፋፋት የተጠቀምናቸውን ዘዴዎች፣ የተገኙ ጥሩ ውጤቶችንና ልምዶችን መውሰድ አስፈላጊ ነው::

በዚህ መሰረት ለአጀማመር የተጠቀምንበት ዘዴና ተሞክሮ እንዲሁም በሀገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በየአካባቢው የሚከናወኑ ተግባራት ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ::

ስለዚህ በመጀመሪያ ከታቀፉት 40 ቤተሰቦች የተገኙትን ተሞክሮዎች በመጠቀም በሁለተኛው ዙር 45፣ በሦስተኛው ዙር ደግሞ 55 ቤተሰቦችን በአራት ወር በማቀፍ በአንድ ዓመት በሁለቱ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች 280 ቤተሰቦች የሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

በሁለተኛው ዓመት 60 አዳዲስ ቤተሰቦችን በየአራት ወር በማቀፍ በአንድ ዓመት ውስጥ በሁለቱ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች 360 ቤተሰቦች የሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ተጠ ቃሚ ይሆናሉ፡፡

በሦስተኛውም ዓመት እንዲሁ 60 አዳዲስ ቤተሰቦችን በአራት ወር በማቀፍ በአንድ ዓመት ውስጥ በሁለቱ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች 360 ቤተሰቦች የሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ስለዚህ በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች በሙሉ ቢበዛ በሦስት ዓመት ውስጥ በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ በመታቀፍ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ሆኖም ግን ፈጣንና መሠረታዊ የጤና ለውጥ ለማምጣት ሁሉንም የሕብረተሰብ አባላት በሞዴል ቤተሰብ ፖኬጅ የማቀፍ ተግባሩ ሦስት ዓመት መውሰድ የለበትም፡፡ ይኸውም "የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ" እንደሚባለው የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ከሰለጠኑ በኋላ በተግባር የሚተገበሩ ጭብጦችን በመጀመሪያ በቤታቸው በመተግበር ለሌሎች የቅርብ ጎረቤቶቻቸው፣ ዘመዶቻቸው ጓደኞቻቸው ጥቅሙን በማስረዳትና በማሳየት የእነሱን አርአያ እንዲከተሉ በማድረግ ኘሮግራሙ የውይይት አጀንዳ እንዲሆን፣ ጥቅሙን በቅርብ እንዲረዱት ያደርጋል፣ በቀላሉ መተማመንም ላይ ደርሰው ተግባራትን እንዲፈጽሙ ያስችላል፡፡

ስለዚህ እያንዳንዳቸው የበጐ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች እቀይራቸዋለሁ፣ አሳምናቸዋለሁ የሚሏቸውን የቤተሰቦች /ቤቶች/ ቁጥር በፈቃደኝነት በመያዝ እራሳቸው የሚተገብሩትን እንዲተገብሩ በማድረግ የሞዴል ቤተሰቦችን ቁጥር እንዲያበዙ ቆጥሮ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ የተሻለ ያከናወኑትንም ማመስገን የምስክር ወረቀት መስጠት መንደሩንም ሆነ በጎ ፈቃደኞችን እንደ ጥሩ ምሳሌ መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡በመሆኑም በጎ ፍቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኛ በማሳተፍ የራሳቸውን ሞዴል ቤተሰብን ቢያንስ ከ5 እስከ 10 ቤተሰብን በመያዝ የተማሩትን በማስተማርና በመተግበር በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕብረተሰቡን የሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል፡፡

### 6.2.4 የሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ተጠቃሚዎች ምረቃ

በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ የታቀፉት ቤተሰቦች የተገበሯቸውን የጤና መልዕክቶች በየስድስት ወሩ በመገምገም የምረቃ ሥነ ሥርዓት ተዘጋጅቶ ለሕብረተሰቡ ምሳሌ እንዲሆኑ የምሥክር ወረቀት በመስጠት ይበረታታሉ፡፡

***ለምረቃ ብቁ ለመሆን የሞዴል ቤተሰቦቹ ማከናወን ያለባቸው ተግባራት***

አንድ ቤተሰብ በጤና አጠባበቅ ፓኬጆች ተግባራዊ በማድረጉ ለመመረቅ የሚከተሉትን ነጥቦች ማሟላት ይኖርበታል፡-

**የመፀዳጃ ቤት መገንባትና በአግባቡ መጠቀም**

- መፀዳጃ ቤትን በንፅህና መያዝ
- ሁሉም የቤተሰብ አባላት አዘውትረው ከተጠቀሙ

- ከተፀዳዱ በኋላ እጅን በሳሙና ወይም በአመድ መታጠብ ከተለመደ
- በመፀዳጃ ቤቱ አካባቢ የእጅ መታጠቢያ ከተዘጋጀ

**የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ተዘጋጅቶ በጥቅም ላይ ከዋለ**

- የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ/ ማቀጠያ ማዘጋጀት ወይም ለኮምፖስት መጠቀም
- የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረጊያ ጉድጓድ ተዘጋጅቶ በጥቅም ላይ ከዋለ

**የመመገቢያ ዕቃዎች ንፅህናቸው ተጠብቆ በትክክል ከተደረደሩ**

- መክደኛ ያለው በቀላሉ ሊታጠብ የሚችል ለስለሳ የምግብ ዕቃ በጥቅም ላይ ከዋለ
- ምግብ ሲዘጋጅና ሲሰራ በንፅህና መያዝ ከተለመደ
- ትርፍራፊ ምግብን ለይቶ ማስቀመጥና እንደገና በደንብ አሙቆ መመገብ ከተለመደ

**የግል ንፅህና**

- ፊትና እጅን ሁልጊዜ መታጠብ
- በሳምንት ቢያንስ አንድ ጊዜ ገላን መታጠብ
- ፀጉርንና ጥፍርን በአጭር መያዝ
- የአፍንና ጥርስን ንጽህና የጠበቁ
- የገላና የልብስ ተበዮችን ያስወገዱ

**የቤትና የአካባቢ ንፅህና በትክክል ከተያዘ**

- የቤትና የቤት አካባቢ ንፅህናናን
- የተለየ ማብሳያ ቤት ያዘጋጁ

- የሰውና የእንስሳት መኖሪያን ከለዩ
- በአካባቢ ቁሳቁስ በመጠቀም የዕቃ መደርደሪያና ምድጃ ከሰሩ
- ቤትን በየጊዜው በመለቅለቅ ሙጃሌንና ሌሎች ተባዮችን ማስወገድ ከተቻለ፣ ነገር ግን በፀረ ወባ ኬሚካል የተረጨን ግድግዳ እስከ ስድስት ወራት ካልተለቀለቀ

## የውሃ አያያዝና አጠቃቀም

- የውሃ መቅጃን ለይቶ ማስቀመጥ ከቻሉ
- ከምንጩ አስተማማኝ ያልሆነ የሚጠጣ ውሃን አፍልቶ ወይም አጠራቶ መጠቀም ከተለመደ
- የቤት ውስጥ ውሃ ፍጆታ ከጨመረ
- የሚጠጣ ውሃ አፉ ጠባብ በሆነ ዕቃ ማጠራቀም ከመጥለቅ መቅዳት ከተለመደ
- የውሃ መቅጃና ማጠራቀሚያ ተለይቶ ከተቀመጠ

## የእናቶችና ህጻናት ጤና አጠባበቅ

- ልጆቻቸውን ከአንድ ዓመት በታች ሙሉ በሙሉ ያስከተቡ ከሆኑ
- ህፃናትን እንደሚገባ የመገቡ ከሆነ
- በቤት ውስጥ ያሉ እናቶች ተገቢውን ያህል የተከተቡ ከሆነ
- የቤተሰብ ዕቅድ ዕውቀት ያሻሻሉ ወይም ተጠቃሚ ከሆኑ
- በቤተሰቡ የታመሙ እናቶችንና ህጻናትን በቶሎ ወደ ህክምና መውሰድ የተለመደ ከሆነ
- ተቅማጥ ለያዘው ህፃን ፈሳሽ ምግቦችን እና ኦ.አር. ኤስ መስጠት ከተለመደ
- ጎጂ ባህሎችን ያስወገዱ ከሆነ

- ነፍሰጡር ሴት በቤተሰቡ ካለች የቅድመ ወሊድ ምርመራ ከሦስት እስከ አራት ጊዜ ካደረገች
- የወሊድ አገልግሎት በሰለጠነ/ች ሙያተኛ ያገኘ ችና ድህረ ወሊድም የምትከታታል(ከወለደች በኋላ ሁለት ጊዜ ምርመራ) አድርጋ ከሆነነ

**ወባን በተመለከተ**

- የአልጋ አጎበር ካላቸው አዘውትረው የሚጠቀሙ ከሆነ
- የወባ ህመም ሲከሰት በፍጥነት ወደ ጤና ድርጅት የሚሄዱ ከሆነ
- በአካባቢ ቁጥጥር በአብዛኛው ተሳታፊ የሚሆኑ ከሆነ

**ኤችአይቪ/ኤድስ**

- ስለመተላላፊያና መከላከያ ዘዴዎች ዕውቀት አሳድገው ከሆነ
- በማህበረሰብ ውይይት ተሳታፊ ከሆኑ
- መድሎና ማግለል የማያደርጉ ከሆነ

**ከተመረቁ ሞዴል ቤተሰቦች የሚጠበቁ ተግባሮች**

- የጀመሯቸውን የጤና ተግባራት አጠናክረው በመቀጠል ለሌሎች አርአያ መሆን
- በወር አንድ ጊዜ እየተገናኙ የልምድ ልውውጥ ማድረግ
- ሕብረተሰቡን በጤና ዙሪያ የማነቃቃትና የማነሳሳት ሥራ መስራት

6.2.5. **የሞዴል ቤተሰብ ተግባርን ቀጣይነት ስለማስጠበቅ**

- በሞዴል የቤተሰብ ፓኬጅ የሰለጠኑና የጤና አጠባበቅ ተግባሮችን ያሻሻሉ ቤተሰቦች ወደ ኋላ እንዳይመለሱና በቀጣይም ተግባራትን ልምድ እንዲያደርጉ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ
- የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ የጤና ሠራተኞች ክትትል፣ ምክርና ማበረታታት በተጨማሪም በጐ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ከሰለጠኑ በኋላ በተግባር የሚተገበሩ ጭብጦች በመጀመሪያ በቤታቸው በመተግበር ለሌሎች ቤተሰቦች አርአያ በመሆን በሥራቸው ለሚታቀፉ የሕብረተሰብ ክፍሎች በማሳተላለፍ እንዲተገብሩ መርዳት፣
- እራሳቸው በመደራጀት እንዲሁም በወጣት በሴቶች ማህበራት እንዲወያዩና የጤና አጠባበቅ ፍላጎቶችን እንዲያሻሽሉ መርዳት ፣
- በየጊዜው ራሳቸውን እንዲያነቃቁ ማበረታታት ፣
- የማህበረሰብ ውይይቶችን በተለያዩ የጤና ርዕሶች ማካሄድ ፣
- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በየወቅቱ በመጎብኘት ማበረታታት ፣
- ህብረተሰቡ ራሱ አካባቢያዊ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን፣ ማህበራትን በመጠቀም ማህበረሰባዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ ፣

## 6.3 ሕብረተሰብ አቀፍ ፓኬጅን ስለማጠናከር

የመከላከሉን ሥራ በተሟላ መልኩ ለመተግበርና በአጠ ቃላይ በህዝቡ ውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት በቀበሌው ውስጥ የሕብረተሰብ አቀፍ ፓኬጅን መስፋፋት ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህም አስፈላጊ የሆኑት ተግባራት

- ሕብረተሰቡ ከእቅድ ዝግጅት እስከ ግምገማ ድረስ እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣
- የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ለማጠናከር የተለያዩ ቦታዎችንና አጋጣሚዎችን /እድር፣ ማህበር፣ የእምነት ቦታዎች፣ ጤና ኬላ፣ ት/ቤት፣ የውኃ ጣቢያ፣ ወዘተ/ መጠቀም፣
- ለፕሮግራሙ ስኬታማነት ሕብረተሰቡ አስፈላጊውን የገንዘብ፣ የጉልበትና የቁሳቁስ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ማስተባበር ፣
- በተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች መካከል ቅንጅታዊ አሠራርን በማስፈን ለቀበሌው የጤና ልማት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማጠናከር ፣
- ሌሎች ቤተሰቦችም በተራቸው በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ስለሚታቀፉ ከወዲሁ ተቀናጅተው የሚሠሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

በዚህ ፓኬጅ የሚጠቀሙ በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ከታቀፉት ውጪ ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ከሥልጠናና ከቤት ለቤት ጉብኝት ውጪ ሌሎችን አገልግሎቶች ያገኛሉ፡፡ በተራቸውም በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ ውስጥ የሚታቀፉ ይሆናሉ፡፡

## 6.4. ከበጐ ፍቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሰራተኞች ጋር አብሮ ስለመሥራት

የበጐ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ተመርጠ ውና ቁልፍ በሆኑ የጤና ጉዳዮች ላይ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ ሕብረተሰቡን በበጐ ፈቃደኝነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ የሚሰጣቸውም ሥልጠናም በቀላሉ በተግባር ላይ ሊያውሏቸው የሚችሉአቸው፣ ተግባራት ላይ አጽንኦት ያደረጉና ጤናማ የባሕሪይ ለውጥ ማምጣት ላይ ያተኰሩ ናቸው፡፡

የበጐ ፈቃደኛ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ስልጠ ናቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ የሕብረተሰባቸው ተመልሰው የተማሩትን ትምህርት መጀመሪያ በየቤታቸው በተግባር በመተርጐም ለሌሎች አርአያነታቸውን ያሳያሉ፡፡ ከዚያም ለጓደኞቻቸውና ለጐረቤቶቻቸው የቀሰሙትን የጤና መልዕክቶች በማስተላለፍ እነሱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዕለት ተዕለት ውሏቸው ለምሳሌ ቡና በሚጠጡበት፣ የወለዱ እናቶችንና የታመሙ ሕፃናትን በሚጠይቁበት ፣ በዕድር ስብሰባዎች፣ ውኃ በሚቀዱባቸው ቦታዎች፣ በገበያ ሥፍራዎችና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ሁሉ ለሕብረተሰቡ አባላት የጤና መልዕክቶቹን ያስተላልፋሉ፡፡ በውሉ ገብ አማካኝነት መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ለማዳረስ የአካባቢውን ሕብረተሰብ ያስተባብራሉ፡፡ የበጐ ፍቃደኛ ሠራተኞች የግል ሕይወታቸውን ስለሚመሩ ሙሉ ጊዜያቸውን ይኸንን ሥራ ብቻ ይሰራሉ ብሎ መጠበቅ አይገባም፡፡ ሆኖም ግን ይብዛም ይነስ

ላበረከቱት አስተዋጽኦ ሊመሰገኑና ሊበረታቱ ይገባቸዋል፡፡

በሀገራችን በእያንዳንዱ ቀበሌ በርካታ የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ የጤና ሠራተኞች በጤና ጥበቃና በሌሎች መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሰለጠኑና የሚደገፉ ናቸው፡፡ እነዚህም የቀበሌ ጤና ተጠሪዎች፣ የሰለጠኑ ልምድ አዋላጆች፣ ማህበረሰብ አቀፍ የሥነ ተዋልዶ ጤና ሠራተኞች፣ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ህሙማን ተንከባካቢዎች፣ የቤት ለቤት የወባ ሠራተኞች፣ ወዘተ በመባል ይጠራሉ፡፡ እነዚህ ሠራተኞች በአንድ ስም የሕብረተሰብ በጎ ፈቃድ ጤና ሠራተኞች (CHW) ተብለው በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች አደራጅነት አብረውና ተባብረው መስራት አለባቸው፡፡ ስለዚህ እነዚህን የጤና ሠራተኞች እያንዳንዳቸው ከ20 እስከ 50 ለሚደርሱ ቤተሰቦች የበጎ ፈቃድ የጤና ሠራተኛ ሆነው ሊያገለግሉ ተጠሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

አንድ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ከ10 እስከ 25 በጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ማደራጀት አለባት፡፡ የሚመረጡት በጎ ፈቃደኞች ከሞዴል የቤተሰብ ፓኬጅ ውስጥ ከታቀፉት የተሻሉ የአፈጻጸም ውጤትና ልምድ ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፡፡ ምርጫውም በህብረተሰቡ ተሳትፎ የሚካሄድ ነው፡፡

የሞዴል ቤተሰብ ፖኬጅ ያልተዳረሰበት የቀበሌ ክፍል ደግሞ የምርጫ ነጥቦች ያሚሉት የሕብረተሰቡ በጐ ፈቃድ ሠራተኞች በሕብረተሰቡ ተመርጠውና ሥልጠና ወስደው እንዲያገለግሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሰራተኞች በሕብረተሰቡ ተሳትፎ ሲመረጡ የሚከተሉት መስፈርቶች ግምት ውስጥ ሊገቡ ይገባል፡፡

- በሞዴልነት የቤተሰብ አቀፍ ፓኬጅን ተግባራዊ የሚያደርጉ
- በፈቃደኝነት ሕብረተሰቡን የሚያገለግሉ
- በሕብረተሰቡ የሚከበሩና የሚደመጡ
- ከ50 በመቶ በላይ ሴቶችና ማንበብና መጻፍ የሚችሉ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡

የተመረጡት የህብረተሰብ በጎ ፈቃድ ጤና ሠራተኞች በአግባቡ ሥራቸውን ማከናወን እንዲችሉ በሞዴል ቤተሰብ ካገኙት ሥልጠና በተጨማሪ በተወሰኑ የጤና ጭብጦችና የመግባቢያ ዘዴዎች ላይ ለሶስት ቀን ማሰልጠን ያስፈልጋል፡፡ ስልጠናው በቤተሰብ ጤና መመሪያ ማንዋል ላይ በተጠቀሰው መሠረት ሆኖ የሚከተሉትን ርዕሶች የሚያካትት ይሆናል፡፡

1. የግልና የአካባቢ ንጽሕና
    - አይነ ምድር /የሕፃናትን ጨምሮ/ በአግባቡ ማስወገድ፣ ከተጸዳዱ በኂላ፣ ምግብ ከማዘጋጀትና ልጆችን ከመመገብ በፊት እጅን በሳሙና ወይም በአመድ መታጠብ፣
    - ልጆችን በየቀኑ ፊታቸውን እንዲታጠቡ ማድረግ ፣
    - ንፁህ የመጠጥ ውሃን መጠቀም ፣

2. የቤተሰብ ጤና ክብካቤ
    - ሕፃናት እንደተወለዱ ከእናታቸው ጋር ገላ ለገላ እንዲገናኙ ማድረግና በተወለዱ በአንድ ሰዓት ውስጥ እንገርን ጨምሮ ጡት መጥባት እንዲጀምሩ ማድረግ፣

- ለሕጻናት እስከ 6 ወራት ድረስ የጡት ወተት ብቻ መስጠትና ቢያንስ እስከ ሁለት ዓመት መቀጠል ፣
- ለሕጻናት ከ6 ወራት እድሜ በኋላ ተጨማሪ ምግብን መስጠት ፣
- ለሕፃናት በቂ የሆነ እንደ ቫይታሚን ኤ፣ ዲ፣ አዮዲን፣ ብረት ያሉ ንጥረ ነገሮችን ከምግባቸው ጋር ወይም በተጨማሪነት እንዲያገኙና በቂ የሆነ የፀሐይ ብርሃን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- ለልጆች ፍላጎት በቂ ትኩረት በመስጠትና አካባቢውን ምቹ በማድረግ አእምሯዊና ማህበራዊ እድገታቸውን ማጎልበት፣
- ለክትባትና ለእድገት ክትትል ልጆችን በጊዜው ወደ ጤና ድርጅት መውሰድ፣
- ልጆች በታመሙ ጊዜ በቤት ውስጥ አግባብ ያለውን ሕክምና መስጠት፣ ተጨማሪ ሕክምና በሚያስፈልጋቸው ወቅት ፈጥኖ መረዳትና ተገቢውን ህክምና ከሰለጠነ ባለሙያ እንዲያገኙ ማድረግ ፣
- ልጆች በሚታመሙበት ወቅት አግባብ ያለው ምፋብና በርከት ያለ ፈሳሽ የጡት ወተትን ጨምሮ መስጠት፣
- የጤና ባለሙያ ምክር፣ የህክምናና የክትትል ቀጠሮን ማክበር፣
- ነፍሰ ጡር ሴቶች ሁሉ የቅድመ ወሊድ ምርመራና በቂ የማዋለድ አገልግሎት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- ወንዶችም ሴቶችም የስነተዋልዶ አገልግሎት እንዲሹ ማበረታታት፣
- ልጆችን ከማንኛውም አደጋ በሚገባ መጠበቅና ጉዳት ሲደርስባቸው በወቅቱ ተገቢውን ህክምና እንዲያገኙ ማድረግ፣

- በልጆች ላይ የሚደረግን እንግልትና ኢ-ሰብአዊ ድርጊትን በጊዜ ማወቅ፣ መከላከልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፣
- ጎጂ የሆኑ ልማዳዊ ድርጊቶችን ማስወገድ /እንጥል ማስቆረጥ፣ ግግ ማስቧጠጥ፣ የሴት ልጅ ግርዛት/፣

3. **የበሽታ መከላከልና ቁጥጥር ዘዴዎች**

- ወባማ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ልጆች በአልጋ አጎበር ውስጥ እንዲተኙ ማድረግና የወባ ትንኝ መራቢያ መንገዶችን ማስወገድ
- ህብረተሰቡ ኤድስን ለመከላከል ለታመሙና ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች አስፈላጊውን እንክብካቤና ድጋፍ ለመስጠት የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ
- ህብረተሰቡ ከኤች አይቪ/ኤድስ ራሱን እንዲጠብቅ መምከር ፣

4. **የጤና አጠባበቅ ትምህርትና የመግባቢያ ዘዴዎች**

- የምክር አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴዎች
- ዘለቄታዊ የሆነ የባሕሪ ለውጥ ማምጣት አስፈላጊነት
- የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም
- የተለያዩ የመልዕክት ማስተላለፊያ መንገዶች አጠ ቃቀም
- የማሕበረሰብ ውይይት አመራር
- ተደራሲያንን ወይም ተሳታፊዎችን መለየት

***ከሰለጠኑ በኋላ ማኅበረሰቡንና ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳት የሚያከናውኗቸው ተግባራት***

- የቤተሰባቸውን ጤንነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ቀለል ያሉና ሊተገበሩ የሚችሉ የጤና ተግባራትን በቤታቸው ውስጥ በማከናወን ለሌሎች የማ ሕበረሰቡ አባላት መልካም አርአያ መሆን
- ቤተሰቦቻቸውን፣ጓደኞቻቸውን፣ ነፍሰ ጡሮችን፣ አዲስ የተወለዱ ሕፃናትን፣ የታመሙ ሕፃናትን በየቤታቸው እየሄዱ ሲጠይቁ መልእክቶችን ማስተላለፍ
- በአካባቢያቸው ለሚያገኟቸው ሰዎችና በቀበሌ የጤና ኮሚቴዎች፣ በድጋፍ ሰጪ ቡድኖች፣ በአምልኮ ቦታዎች፣ በቀይ መስቀል፣ በኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ በደቦና መሰል የጋራ ሥራዎች፣ በእድር፣ በቡና ጠጡ ሥነ ስርዓትና በመሳሰሉት ማኅበራዊ ግንኙነቶች ወቅት መልእክቶችን ማስተላለፍ
- የማሕበረሰቡ አባላት በቀበሌ ስብሰባዎች፣ በገበያ ቀኖችና በአካባቢው በአዓላት ቀን ሲሰባሰቡ ስለጤና በማወያየት
- ማሕበረሰቡን ለውሎ ገብ የጤና አገልግሎት በማስተባበር፣ ለተለያዩ የጤና ዘመቻዎች ወይም በክሊኒክ ህክምና ለማግኘት ልጆቻቸውን ይዘው መምጣታቸውን ማረጋገጥ

- ለጤና ሥራዎች ሕብረተሰቡን መቀስቀስና ማስተባበር፣ ያስተባብራሉ፡፡
- ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ጋር በመሆን በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚሰሩ የጤና ተግባራትን ማቀድ፣ መተግበር፣ የተሰሩ የጤና ሥራዎችንም ለጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ሪፖርት ማድረግ፡፡

የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች የሚሰሩት የጤና ሥራ የተቀናጀ፣ የታቀደና ውጤታማ እንዲሆን ከጤና ኤክስቴሽን ሠራተኞች ማበረታቻና ድጋፍ ያስፈልጋል:: የመደጋገፉና የማበረታታቱ ሥራ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊከናወን ይገባል::

- በየወሩ አጭር የልምድ ልውውጥ ስብሰባዎችን እንደአመቺነቱ በየንዑስ ቀበሌው ወይም በቀበሌው በማድረግ፣
- በስብሰባዎች ወቅት በጎ ፈቃደኞች ያጋጠሟቸውን ችግሮች በመፍታት፣ ለሰሯቸው ሥራዎች እውቅና በመስጠት፣
- በጎ ፈቃደኛ መሆናቸውን ተገንዝቦ ለሰሩት ማንኛውም ሥራ ምሥጋና በማቅረብ፣
- በጎ ፈቃደኞች በራሳቸው ዕቅድ ላይ ለመመወያየት ጊዜ እንዲወስኑና እንዲገናኙ በማድረግ ፣
- በጎ ፈቃደኞች የሰሯቸውን ሥራዎች በመጎብኘት፣
- በዓመት አንድ ጊዜ በጎ ፈቃደኞች ያስገኟቸውን ውጤቶች ሕብረተሰቡ እንዲያውቅ ከቀበሌ አስተዳድር ወይም ከጤና ድርጅት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ማድረግ ናቸው::

## 6.5 የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የሥራ ስምሪት

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች 75% የሚሆን ጊዜያቸውን ከጤና ኬላ ውጪ ለመስክ ስራ መመደብና መስራት ይገባቸዋል:: በዚህ መሰረት ሕብረተሰቡን በማሳተፍ ሳምንታዊ ፕሮግራም ማውጣትና ማሳወቅ አለባቸው:: ስለዚህም፤

- የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞቹ የት እንደሆኑ የሚያመላክት በጤና ኬላው በር ላይ መለጠፍ::

- ከ3-4 የውሎ ገብ ጣቢያዎችን በማቋቋም በሳምንት አንድ ጊዜ አገልግሎት መስጠት፡፡
- ጤና ኬላውን በየቀኑ አንዳቸው እስከ ሁለት ሰዓት ለአገልግሎት ክፍት ማድረግ፡፡
- የቤት ለቤት ጉብኝት በማድረግ በሞዴል ቤተሰብ ፓኬጅ የታቀፉትን አገልግሎት መስጠት፡፡
- በቀበሌ ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሳምንታዊ ፕሮግራም በማውጣት የጤና ትምህርት መስጠትና ሰርቶ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በቤት ለቤት ጉብኝት፣ በውሎ ገብ ጣቢያና በትምህርት ቤት እንዲሁም በጤና ኬላ የሚሰ ጡት አገልግሎት እቅድና የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀትና የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች፣ ቼክ ሊስትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመያዝ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ማስተማርና ሠርቶ ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡

<u>በቤት ለቤት ጉብኝት የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች</u>

- የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ሰርቶ ማሳየት
- የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ማስተማርና ማሳየት
- የግል ንጽህና አጠባበቅ ማስተማርና ማሳየት
- የመጸዳጃ ቤት አያያዝና አጠቃቀምን እንዲያሻሽሉ መርዳት
- የቤት ውስጥና የቅጥር ግቢ ንጽሕና አጠባበቅ
- የመኖሪያ ቤትንና የከብቶች ማደሪያን እንዲለዩ መምከር
- የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት መስጠት
- የቅድመ ወሊድ ክትትል፣ የወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት ምክር መስጠት
- የጨቅላ ህጻን መሠረታዊ ክብካቤን ማሳየት

- የህጻናት እድገት ክትትልና ማድረግና ስለአመጋገብ መምከር
- የሕጻናትና የነብሰ ጡር እናቶች የስነ-ምግብ እጥረት ልየታና የምክር አገልግሎት መስጠት
- በወባማ ቦታዎች የወባ ትንኝ የሚያራቡ ቁሳቁሶችን ማስወገድና ያቋሩ ውሃዎችን እንዲያፋስሱ መምከር
- በወባማ ቦታ የአጐበር አጠቃቀምን ማየትና በትክክል እንዲጠቀሙ ማሳየት
- በወባ የታመሙ ቤተሰቦችን ማከም
- የቴትራሳይክሊን ቅባትን በመጠቀም የትራኮማ በሽታን ማከምና ስለፊት መታጠብ ማስተማር
- የእከክ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር
- የተቅማጥ በሽታ ለያዘው ፈሳሽ ምግቦችና ኦ.አር.ኤስ መስጠት
- የታመሙ ቤተሰቦችን በመለየት ወደ ቀጣዩ ጤና ተቋም እንዲሄዱ ማድረግ
- ቫይታሚን ኤ ለሚያስፈልጋቸው መስጠት
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ማድረግ
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና የቲቢ ህሙማንን መከታተል
- የህብረተሰብ በጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞችን በተግባር ማስተማር፣ ማስተባበር፣ የሰሯቸውን ሥራዎች መጎብኘትና ማበረታታት
- የኤድስ ህሙማን ክብካቤ እንዲሁም የወላጅ አልባ ሕፃናት ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- አስፈላጊ መረጃዎችን መመዝገብ

<u>በውሎ ገብ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች</u>

- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት
- የክትባት አገልግሎት ለሕፃናትና እናቶች መስጠት
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት
- የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግና መምከር

- የሕጻናት እድገት ክትትል መስራትና መምከር
- የሕጻናትና የነብሰ ጡር እናቶች የሰነ-ምግብ እጥረት ልየታና የምክር አገልግሎት መስጠት
- በወባማ ቦታ ወባን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ማከናወን
- የቴትራሳይክሊን ቅባትን በመጠቀም የትራኮማ በሽታን ማከምና ስለፊት መታጠብ ማስተማር
- የእከክ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር
- የተቅማጥ በሽታ ለያዘው ኦ.አር.ኤስ መስጠት
- ቫይታሚን ኤ ለሚያስፈልጋቸው መስጠት
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ማድረግ
- የታመሙ  ሕጻናትም ሆነ ሌሎች ህሙማንን በመለየት ወደ ቀጣዩ የጤና ተቋም እንዲሄዱ ማድረግ
- በትምህርት ቤት ፕሮግራም በማዘጋጀት የጤና አጠ ባበቅ ትምህርት መስጠትና ሰርቶ ማሳያዎችን መስራት

## በጤና ኬላ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶች

- የጤና አጠባበቅ ትምህርት መስጠት
- የክትባት አገልግሎት ለሕፃናትና እናቶች መስጠት
- የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስጠት
- የቅድመ ወሊድ ክትትል ማድረግና መምከር
- የወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎትና ምክር መስጠት
- የሕጻናት እድገት ክትትል መስራትና መምከር
- የሕጻናትና የነብሰ ጡር እናቶች የሰነ-ምግብ እጥረት ልየታና የምክር አገልግሎት መስጠት
- ወባን የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባር ማከናወን
- በተቅማጥ በሽታ ለተያዙ ኦ.አር.ኤስ መስጠት
- የቴትራሳይክሊን ቅባትን በመጠቀም የትራኮማ በሽታን ማከምና ስለፊት መታጠብ ማስተማር
- የእከክ በሽታን መከላከልና መቆጣጠር

- ለታመሙ ሕጻናት ወይም ለሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊ እርዳታ ማድረግ፣ ከአቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ወደ ቀጣዩ የጤና ተቋም መላክ
- ቫይታሚን ኤ ለሚያስፈልጋቸው መስጠት
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ማድረግ
- ከበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ጋር ቋሚ የሆነ መደበኛ ስብሰባ ማካሄድ፣ እንደአስፈላጊነቱ ስልጠና መስጠት
- የተከናወኑ ስራዎችን መመዝገብ፣ ፋይል ማደራጀት፣ መረጃን ማጠናቀርና ሪፖርት ማቅረብ
- አስፈላጊ መረጃዎችን በግራፍና በቻርት በመስራት ግድግዳ ላይ መለጠፍ

## 7. በቀበሌ ደረጃ ቅንጅታዊ አሠራር

ቀበሌ ዝቅተኛ አስተዳደር እርከን እንደመሆኑ መጠን ሁሉንም የልማት ሥራዎች በቅንጅት ለማስኬድ የተሻለ ነው፡፡ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራምን ስኬታማ ለማድረግ በቀበሌው ውስጥ ከሚገኙ ከግብርናና ገጠር ልማት፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከውሃ ሀብት ልማት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከሕዝባዊ ማሕበራት፣ ወዘተ. ጋር አብሮ ማቀድ፣ ተግባራዊ ማድረግ መከታተልና መገምገም እንዲቻል የጋራ መድረክ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

የቅንጅታዊ አሠራሩንም በየጊዜው መገምገምና የቀበሌው አስተዳደር ተገቢውን እርምጃ  መውሰድ አለበት፡፡ በተለይ በግብርና ልማት ኤክስቴንሽን በቤተሰብ ውስጥ የሚሰጡ ፓኬጆች ስላሉ ከነሱ ጋር አብሮ ማቀድ ያስፈልጋል፡፡ በትምህርት ቤት በኩልም ከትምህርት ቤት አስተዳደር ጋር በመነጋገርና በቅድሚያ ስለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም መምህራንን በማሰልጠን ፍላጐት ያላቸውን ተማሪዎች እንዲመርጡ፣ ለተማሪዎች ስልጠ

ናውን እንዲሰጡ፣ ተማሪዎችም ወደ ቤተሰብ ሄደው ተገቢውን ትምህርት በመስጠት ቤተሰቦቻቸው ሞዴል ቤተሰብ እንዲጀመሩ ማድረግ ይችላሉ፡፡ በት/ቤቶች ውስጥ የጤና ትምህርት አስፈላጊነት በማስረዳት ለተማሪዎች አስፈላጊና ወቅታዊ የሆነ የጤና ትምህርት በመስጠት መልዕክቶችን ወደ ቤተሰብ ማዳረስ ይቻላል፡፡

## 8. የግብዓት አቅርቦት ሥርዓትን ስለማደራጀት

የጤና ኤክስቴንሽን በፕሮግራሙ የታለመውን ግብ እንዲመታ ሁሉም አካላት በግብአት አቅርቦት ዙሪያ የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ ለዚህም ሀብትና ጉልበት እንዳይባክን በቅንጅት መስራት ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ለጤና ኬላዎች የሚያስፈልገውን ግብአትና ያለውን ችግር ለይቶ በመረዳት ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በትክክለኛው ጊዜ፣መጠንና ጥራት መሰረት ማቅረብ ለሚሰጠው አገልግሎት ጥራት እንዲሁም ለባለሙያው ሞራል ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም የግብአት አቅርቦት ሥርዓት አደራጅቶ በስራ ላይ ማዋል ይገባል፡፡ በአጠቃላይ ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለማሟላት አስፈጻሚ /ፈጻሚ አካላት ሊያከናውኗቸው የሚገባቸው የየራሳቸው ተግባራት አሉ፡፡ እነዚህም፡-

**በፌዴራል ደረጃ**

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሚያስፈልጉ የሕክምና መገልገያዎችን፣ቁሳቁሶችንና ማጣቀሻ መጻሕፍትን፣ ወዘተ. ከጤና ኬላዎችና ከጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች ቁጥር ጋር በተገናዘበ መልኩ ለማቅረብ ከክልል ጤና ቢሮዎችና

ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር የግብአት አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋትና የህብት ማፈላለግ ሥራ ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

**በክልል ደረጃ**

የክልል ጤና ቢሮ ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራርን የማስፈን፣ ግብአትን በደረጃው የማፈላለግ፣ የሰው ኃይል ስልጠናና የሕክምና መገልገያዎችን፣ መድኃኒቶችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ማሟላት፤ የጤና ኬላዎች ግንባታ እንዲካሄዱ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

**በዞን ደረጃ**

የዞን ጤና መምሪያ ከመንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ቅንጅታዊ አሰራርን የማስፈን፣ ግብአትን በደረጃው የማፈላለግ፣ የሰው ኃይል ስልጠናና የሕክምና መገልገያዎችን፣ መድኃኒቶችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ማሟላት፤ የጤና ኬላዎች ግንባታ እንዲካሄዱ በወረዳ ደረጃ የግብአት አቅርቦት ስርዓቱን ለማጠናከር ቅንጅታዊ አሰራርን በማስፈን ኃላፊነት መወጣትአለበት፡፡

**በወረዳ ደረጃ**

የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በወረዳ ደረጃ የግብአት አቅርቦት ስርዓቱን ለማጠናከር ቅንጅታዊ አሰራርን በማስፈን ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ በጀት እንዲመደብ ማድረግ፣ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችንና መድኃኒቶችን ማሟላት፣ የመረጃ ፍሰትን ማጎልበት፣ ሕብረተሰብ አቀፍ የሆኑ ድርጅቶችን ተሳትፎ ማጠናከርና ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ ለግብአት አቅርቦቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ማስተባበርና አመራር መስጠት ይኖርበታል፡፡

ለጤና ኬላ የሚያስፈልጉ የክትባትና የህክምና ቁሳቁሶች እንዲሁም መድኃኒቶች አቅራቢያ ወደሚገኘው ጤና ጣቢያ ወይም አዳጊ ጤና ጣቢያ ማድረስ አለበት፡፡

**በቀበሌ ደረጃ**

የቀበሌ አስተዳድር በቀበሌው በሚገኙ የልማት ድርጅቶች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር በማስፈን ሕብረተሰቡ በጉልበት፣ በቁሳቁስ፣ በገንዘብ፣ በሐሳብ እንዲሳተፍ ማድረግ፣ ለመንግሥት ንብረት ተገቢውን ጥበቃ የማድረግና የግብአቶች አጠቃቀም በቁጠባ መሆኑን የማረጋገጥ ተግባር ይጠበቅበታል፡፡ ለጤና ኬላ የሚያስፈልጉ የክትባትና የህክምና ቀሳቁሶች እንዲሁም መድሃኒቶች ከአቅራቢያ ጤና ጣቢያ የሚመጣበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡ ከዚህ ሌላ በጤና ኬላ ደረጃ የሚከተሉትን ሥራዎች ማከናወን አለበት፡፡

- የግብአት አያያዝ ሥርዓቱን ተከትሎ መሥራት
- ያለቁትንና ጊዜያቸው ያለፈባቸውን በመለየት ማስቀመጥ
- የሚያስፈልጉትን ግብአቶች በመለየት በወቅቱ ጥያቄ ማቅረብ
- የመድሃኒትና የቁሳቁስ መከታተያ ካርድ መጠቀም
- በየሩብ ዓመቱ የንብረት ምዝገባና ቆጠራ በማካሄድ ለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤትና ለአቅራቢያ ጤና ጣቢያ ሪፖርት መላክ፣

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ ከላይ ያሉትን ስርዓቶችና እንዲሁም የተጠቃሚውን ፍላጐትና ፍጆታ መሠረት በማድረግ ለጤና ኬላው የሚያስፈልገውን ግብዓት በተመለከተ ለወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በየሩብ አመቱ መጠይቅ ታቀርባለች፡፡ የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤትም ጥያቄውን መሠረት በማድረግ ለአቅራቢያው ለሚገኘው

ጤና ጣቢያ /አስኳል/ታዳጊ ጤና ጣቢያ/ ይልካል:: የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛም ከጤና ጣቢያ በቀበሌ አመራር አጋዥነት አስፈላጊውን ግብአቶች ተረክባ ወደ ጤና ኬላው ትወስዳለች:: አላስፈላጊ የመድኃኒት ክምችት እንዳይኖር በየጊዜው ክትትል ማድረግ፣ የመጠቀሚያው ጊዜ ከማለፉ በፊትም ጥቅም ላይ እንዲውል ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል:: የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ሊያልፍ የተጠጉ መድኃኒቶችን ግን ጊዜያቸው ከማለፉ በፊት በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤትና ለአቅራቢያ ጤና ጣቢያ ማሳወቅ አለበት::

## 9. የሕሙማን አቀባበልና አላላክ ሥርዓት

በሀገራችን የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች የአደረጃጀት ሥርዓት በአራት እርከን ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ድረስ ተደራጅቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል:: ይህም አደረጃጀት ሕብረተሰቡ ብቃትና ጥራት ያለውን የጤና አገልግሎት በየደረጃው ማግኘት እንዲችል ታስቦ የተቀየሰ ነው::

በዚህ አደረጃጀት ስርዓት መሠረት ጤና ኬላና ጤና ጣቢያ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ናቸው:: ይህም አንድ የጤና ጣቢያና በሥሩ የሚገኙትን አምስት የጤና ኬላዎች የሚያካትት ሲሆን በአጠቃላይ ለ25,000 ሕዝብ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የተደራጀም ነው::

በመሆኑም ሕብረተሰቡ ለቀላል የጤና ችግሮች ብዙ ሳይለፋ በአካባቢው በሚገኙ የጤና ኬላዎችና የጤና ጣቢያዎች የጤና አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል አደረጃጀት ነው:: ሁኔታው ከአቅም በላይ ሆኖ የተሻለ የምርመራና የሕክምና አገልግሎት ሲጠይቅ ግን ወደ

ሚቀጥለው ከፍተኛ የእርከን ደረጃ በመላክ ተገቢውን አገልግሎት ማድረግ ይገባል።

ይሁን እንጂ በሀገራችን የጤና ተቋማት ቁጥር ገና ውስን በመሆኑና ሥርጭታቸውም ሚዛኑን የጠበቀ ባለመሆኑ የቅብብሎሹን ስርዓት እንደተጠበቀው ተግባራዊ ለማድረግ አልተቻለም። በመሆኑም በተለይ በመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም ይህንን ችግር ለመፍታት እንዲያስችል አስኳል (ታዳጊ) የጤና ጣቢያዎችን ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በዚሁ መሠረት የአስኳል ጤና ጣቢያዎች ግንባታ ሥራ እንዲፋጠን በክልልና በወረዳ ደረጃ ከፍተኛ ጥረት ይጠበቃል። የቀበሌ አስተዳደር ደግሞ ከሕብረተሰቡ ጋር በመተባበር ለሕሙማን አቀባበልና አላላክ ሥርዓት ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ ሕብረተሰቡ አገልግሎቱን ያለ ችግር እንዲያገኝ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በየእርከን ደረጃው የሚገኙት የጤና ተቋማት የጋራ ዓላማቸውን በጋራ ጥረት ለማሳካት እንዲችሉ በመካከላቸው መኖር የሚገባውን ግንኙነት በመረዳዳትና በመደጋገፍ ላይ መመሥረት ይኖርባቸዋል። በመሆኑም የጤና አገልግሎቱን የአደረጃጀት ሥርዓት ተከትሎ በማዕከልና በመካከለኛ የእርከን ደረጃ የሚገኙት ተቋማት ባለሙያዎች በመጀመሪያ የእርከን ደረጃ ለሚገኙት ተገቢውን ድጋፋዊ ክትትል፣ የግብረመልስና የስልጠና ድጋፍ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ የህሙማን አቀባበልና አላላክ በሚመለከት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባታል።

- ስለእያንዳንዱ ህመምተኛ ትክክለኛ መረጃ መያዝ
- የህሙማን መላኪያ ቅጾች ማዘጋጀት

- ከጤና ኬላ አገልግሎት በላይ የሆኑትን ህሙማን ያለምንም መዘግየት ወደ አስኳል ጤና ጣቢያ ከበቂ መረጃ ጋር መላክ
- ህመምተኛውን ለመከታተል ያመች ዘንድ ከአስኳል ጤና ጣቢያ ሲመለስ ግብረ መልስ ይዞ እንዲመጣ ለህመምተኛው በቃል ማሳሰብ፣ ለአስኳል ጤና ጣቢያውም በጽሑፍ ግብረመልሱን እንዲልክ መጠየቅ
- በግብረመልሱም መሠረት የህመምተኛውን ቀጣይ ሁኔታ መከታተል
- የተሰጠውን መድኃኒት መጨረሱን ማረጋገጥ የተሰጠውን ምክር ተግባራዊ ማድረጉን መከታተል
- በወርሃዊ ሪፖርት የተከናወኑ የህሙማን ቅብብሎሽ ብዛት ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 10. ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ቀጣይነትን ስለማረጋገጥ

ክትትልና ቁጥጥር ለማካሄድ ፕሮግራሙን የሚመራ አካል መኖሩ አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው /በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረደና በቀበሌ/ የጤና ኤክስቴንሽን ሥራን እንደቁልፍ ተግባር በመውሰድ የድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግ መዋቅር መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

በመዋቅሩ ያሉ ሙያተኞች ኃላፊነታቸውን በተገቢው መወጣት እንዲችሉ በየደረጃው ያሉት የመስተዳድር አካላትና የጤናው ሴክተር ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ሊያግዟቸው ይገባል፡፡ ሁሉም የሥራ ክፍሎች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ በተፈለገው ሁኔታ መከናወኑን ለማረጋገጥ በተከታታይ ድጋፋዊ ጉብኝት፣ ክትትልና ቁጥጥር በቅንጅት ማካሄድ አለባቸው፡፡

በዚህ መሠረት በተለይ በወረዳ ደረጃ ይህ አካል ጠንካራ መሆን ስለሚገባው  በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የሚመራ ከጤና ጣቢያ ያሉ ሙያተኞች ያሳተፈ አንድ አካል መቋቋም አለበት፡፡ ይህ አካል በቀበሌ ደረጃ ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር ሲያደረግ የቀበሌ መስተዳደር፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች፣ የሕብረተሰብ የበጎ ፈቃድ ጤና ሠራተኞችና ሌሎች የልማት ሠራተኞች ከሕበረተሰቡ ጋር በመተባበር የተሠሩትን ሥራዎችና ያጋጠሙ ችግሮች በጋራ ይገመግማሉ፤ ድጋፍም ይሰጣሉ፡፡ በሌሎችም ደረጃዎች የሚደረገው ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር ደረጃውን የጠበቀና አስተማሪነት ያለው መሆን አለበት፡፡

ሕብረተሰቡ የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም እንደ ራሱ ጉዳይ አድርጎ እንዲወሰድ የሚያስፈልገው ክትትል፣ እገዛና ትምህርት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር ክትትሉ የተሟላ እንዲሆን ምን ታቀደ? ምንስ ተሰራ? ምንስ ለውጥ ተገኘ? ብሎ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

በመሆኑም መደበኛው የጤናው ሴክተር አጠቃላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት እንዳለ ሆኖ መንግስት ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ከሰጠው ልዩ ትኩረት አንጻር በየደረጃው የሚከተሉት የክትትልና ግምገማ ተግባራት መከናወን ይገባቸዋል፡፡

- **በቀበሌ ጤና ኰሚቴ ደረጃ**

  የቀበሌ ጤና ኰሚቴ፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞችንና የበጎ ፈቃድ የሕብረተሰብ ጤና ሠራተኞች ባሳተፈ መልኩ በሳምንት አንድ ጊዜ ስብሰባ በማድረግ በፕሮግራሙ አፈፃፀም ላይ ውይይትና ግምገማ በማካሄድ ሪፖርቱን ለቀበሌው ካቢኔ ያቀርባል፡፡ ህብረተሰቡም በሕዝባዊ ስብሰባዎች የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አፈጻጸም በመገምገም

ጠንካራና ደካማ ጐኖችን በመለየት የሚጠ ናከርበትንና የሚሻሻልበትን መንገድ ያመቻቻል፡፡

- **በቀበሌ ካቢኔ ደረጃ**

በቀበሌ አስተዳደር ተማክሎ እንዲታቀድ ክትትል እንዲደረግና ሪፖርትም በጊዜው እንዲደርስ የቀበሌው አስተዳደር የጤና ኤክስቴንሽን እንደ ቁልፍ ስራው ሊወስድ ይገባል፡፡ ስለዚህ የቀበሌው ካቢኔ በየሁለት ሳምንቱ በመሰብሰብ የቀበሌ ጤና ኰሚቴው በአቀረበው ሪፖርት ላይ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ለጤና ኰሚቴው ይሰጣል፡፡ በሌላ በኩል የቀበሌው ካቢኔ የቀረበውን ሪፖርትና ግብረመልስ በማጠናቀር ለወረዳው ካቢኔና በግልባጭ ለወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በየወሩ ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም የሕብረተሰቡን ተሳትፎና የብዙኃን ድርጅቶችን /የወጣቶች፣ የሴቶች ማሕበራት/ የሥራ ሁኔታ እንቅስቃሴ በመስክ ሥራ ጉብኝት በማካሄድ በየ15 ቀኑ መገምገምና ግብረመልስ መስጠት አለበት፡፡

- **በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ደረጃ**

በወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የሚመራ ከጤና ጣቢያ/ታዳጊ ጤና ጣቢያ/ ያሉ ሙያተኞችን ያካተተ ቡድን በማደራጀት በወረዳ ውስጥ ያሉትን ቀበሌዎች በመከፋፈል በየወሩ በመስክ በመገኘት ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ያጋጠሙ ችግሮችን ይገመግማሉ፣ ድጋፍም ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪም የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ከጤና ኬላ የሚደርሰውን ሪፖርትና በመስክ ጉብኝት የተገኘውን ውጤት በማጠናከር በየወሩ በመሰብሰብ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ለቀበሌው ካቢኔ/ጤና ኬላ/ ይሰጣል፡፡

በሌላ በኩል የቀረበውን ሪፖርትና የተሰጠውን ግብረመልስ በማጠናቀር በዞን ጤና መምሪያ በኩል ሪፖርቱን ለክልል የጤና ቢሮ ያቀርባል፡፡

- በየወሩ በሚደርሰው ሪፖርት መሠረት አጭር ግምገማ ያካሄዳል፡፡
- የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የጤና ኬላዎችን ቢያንስ በሦስት ወር አንድ ጊዜ መጐብኘት ይጠበቅበታል፡፡
- ጉብኝቱ በቼክ ሊስት የተደገፈ መሆን ይኖርበታል፣ ከጉብኘቱ በኋላ ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡
- የሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸምን ይገመግማል፣ጥሩ ሥራን ያበረታታል፡፡
- ሪፖርት አጠናክሮ በየሩብ ዓመቱ ለወረዳ አስተዳደር እና ለዞን ጤና ጥበቃ መምሪያ ይልካል፡፡

- **በወረዳ አስተዳድር ደረጃ**

ከወረዳ ጤና ጽ/ቤትና ከቀበሌ አስተዳድር የሚደርሰውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ፣ በመስክ በመገኘትና ክትትል በማድረግ በየሩብ ዓመቱ ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አስፈላጊውን ድጋፍና አመራር መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

- **በዞን ጤና መምሪያ ደረጃ**

በየሶስት ወሩ ከወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት እንዲሁም ከመስክ ጉብኝት የሚገኙ ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ከወረዳው ጤና ጥበቃ በተላከው ሪፖርት ላይ ሰፋ ያለ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ለወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ይሰጣል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም አጠር ያለ ወርሃዊ ክትትል እና ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በተመሳሳይ የቀረበውን ሪፖርትና የተሰጠውን ግብረመልስ በማጠ ናቀር ለክልል የጤና ቢሮ ያቀርባል፡፡

- **በክልል ጤና ቢሮ ደረጃ**

  በየሶስት ወሩ ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል፡፡ የክልል ጤና ቢሮ በየሶስት ወሩ በመሰብሰብ ከወረዳው ጤና ጥበቃ/ዞን ጤና መምሪያ/ በተላከው ሪፖርት ላይ ውይይትና ግምገማ በማድረግ ተገቢውን ግብረመልስ ለወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት/ለዞን ጤና መምሪያ/ ይሰጣል፡፡ በተመሳሳይ የቀረበውን ሪፖርትና የተሰጠውን ግብረመልስ በማጠናቀር ለክልል መስተዳድር ካቢኔና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሪፖርት ያቀርባል፡፡

- **በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ደረጃ**

  የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በየሁለት ወሩ በመሰብሰብ የክልል ጤና ቢሮዎች ባቀረቧቸው ሪፖርቶች ላይ ውይይትና ግምገማ ያደርጋል፡፡ በየሶስት ወሩ ከክልል የቀረበውን ሪፖርት ያጠናክራል፣ ድጋፍና ግብረመልስም ይሰጣል፡፡ በየስድስት ወሩም በመስክ በመገኘት ለጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ድጋፋዊ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም አደረጃጀት

የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በተጠናከረ መልኩ ለመተግበርና ለመከታተል እንዲቻል በፌዴራል ጤና በቃ ሚ/ር ደረጃ የጤና አጠባበቅ ትምህርት ማዕከልን መልሶ በማደራጀት በማዕከሉ ውስጥ የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም በመምሪያ ደረጃ ተዋቅሮ ስራዎችን እንዲያስተባበር ተደርጓል፡፡

በክልል ጤና ቢሮዎች ደረጃም የጤና ኤክስቴንሽን ኘሮግራም የሚያስተባብር እንደ ክልሉ ስፋትና ተጨባጭ ሁኔታ በመምሪያ /በአገልግሎት ወይም በቡድን/ ደረጃ እየተዋቀረ ሲሆን በወረዳ ደረጃም ራሱን የቻለ መዋቅር እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡

በየደረጃው ማለትም በፌዴራል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ኘሮግራሙን ከማስተባበር፣ ከመከታተል፣ ከተጠያቂነትና ሪፖርት ከማድረግ፣ ወዘተ. አኳያ መዋቅሩ አስፈላጊነቱና ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ ይታመናል፡፡

"ሁሉም መንገድ ወደ ጤና ኤክስቴንሽን ያመራል" በሚለው መርህ መሠረትም ሌሎች እያንዳንዳቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ የሥራ ክፍሎች ኘሮግራሙን እንደ ቁልፍ ተግባር በመውሰድ በዕቅዳቸው አካተው መሥራት አለባቸው፡፡ በመሆኑም ሁሉም በየደረጃው ያሉ አካላት የኤክስቴንሽን ሥራን በመሥራት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# 11. የጤና ኤክስቴንሽን ስራዎች ተፈፃሚነት ደረጃና መለኪያዎች

| ተቁ | የስራ ዓይነት | የስራዎች ተፈፃሚነት ደረጃዎች | | | ስራው በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርጋቸው | የማስተማሪያ ዘዴ | መለኪያ/ኢንዲኬተር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቀላሉ የሚፈፀሙ | መካከለኛ ተፈፃሚ | ለመፈፀም የሚከብዱ | | | |
| 1 | የግልና አካባቢ ንፅህና | | | | | | |
| | 1.1 የግል ንፅህና | ፊትና እጅን በሳሙና ዘወትር መታጠብ፣ በሳምንት አንድ ጊዜ ገላን መታጠብ፣ ፀጉርን በንጽሕና መያዝ፣ጥፍርን መቁረጥ፣ አፍና ጥርስን በንፅህና መጠበቅ | የገላና የልብስ ተባዮችን ማስወገድና መከላከል | የሌሊትና የቀን ልብሶችን መለየት | ህፃናትንና እናቶችን | 1. አጋዥ የማስተማሪያ ማቴርያሎችን መጠቀም<br>2. በአካባቢው የሚገኙትን ሞዴል ቤተሰቦችን መጠ የቅና በአስተማሪነት መጠ ቀም<br>3. የልምድ ልውውጥ<br>4. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ፊታቸውን ያልታጠቡ ህፃናት ብዛት<br>2. በአካባቢው የእከክ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ብዛት<br>3. በትራኮማ የተያዙ ሰዎች ብዛት<br>4. የጤና ትምህርት የተሰጣቸው ሰዎች ብዛት |
| | 1.2 የቤት ንፅህና | 1. የቤትንና የአካባቢ ፅዳት በየቀኑ ማካሄድ | 1.ከዲዲቲ መርጨት ጋር በማይጋጭ መልኩ ቤትን በየሁለት ዓመቱ መቀባት<br>2. የአካባቢው ማቴሪያል በመጠቀም የእቃ መደርደሪያና ምድጃን መስራት | 1.የተለየ ማዕድ ቤት<br>2. የሰውና የእንስሳት መኖሪያን መለየት<br>3. የመኖሪያ ቤት ሲሰራ በቂ ብርሃንና አየር በሚያስገባ መልኩ ማድረግ | የእናቶች፤ ለአቅመ አደምና ሄዋን የደረሱትንና አባወራ | 1. ትምህርት መስጠት<br>2. የልምድ ልውውጥ<br>3. ሰርቶ በማሳየት<br>4. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ከተባዮች ከቁንጫና ከቱሃን ነፃ የሆኑ ቤተሰቦች ብዛት<br>2. የእንስሳትና የሰው መኖሪያን የለዩ ቤተሰቦች ቁጥር<br>3. የማእድ ቤትን ለይተው የሰሩ ቤተሰቦች ብዛት |
| | 1.3 የምግብ ንፅህና | 1. መክደኛ ያለው የምግብ ማስቀመጫ እንዲኖር ማድረግ<br>2. ምግብ ሲሰራና ሲቀርብ በንፅህና መጠበቅ<br>3. የምግብ ማቅረቢያ እቃዎች ንፅህና መጠበቅ<br>4. ምግብን በተመረጠ ቦታ ማስቀመጥ | 1. ወተትን አፍልቶ ጥሬ ስጋን አብስሎ መመገብ<br>2. . የምግብ አያያዝን ፕሪዘርቬሽን መተገበረ | | እናቶችንና ለአቅመ ሄዋን የደረሱትን | 1.የጤና ትምህርት<br>2.ሰርቶ ማሳየት<br>3. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ወተት አፍልተው የሚጠጡ ቤተሰቦች ብዛት<br>2. ጥሬ ሥጋ የሚበሉ ሰዎች ቁጥር<br>3. በምግብ መመረዝ የሚመጡ በሽታዎች መቀነስ |
| | 1.4 ንፁህ ውሃ | 1. የውሀ መቅጂያን ለይቶ በንጽህና ማስቀመጥ<br>2. የውሀ መያዣን ከድኖ ማስቀመጥ<br>3. የውሀ መያዣን ንፁህ ማድረግ | 1. የውሀ ምንጮችን ማጠርና ማስከበር<br>2. የውሃ ጉድጓዶችን ክዳን እንዲኖራቸው ማድረግ<br>3. የውሃ ጉድጓዶች ከመፀዳጃ ጉድጓድ ጋር በማይገናኝ መልኩ ማዘጋጀት | 1. የሚጠጣ ውሃን አፍልቶ መጠ ቀም<br>2. ምንጭን ማጎልበት<br>3. በቂ የውሀ አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ | አዋቂዎችን | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የልምድ ልውውጥ<br>3. ሰርቶ በማሳየት<br>4. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. በማታዩት ውሀ ወለድ በሽታዎች ላይ ለውጥ ማምጣት<br>2. የውኃ መቅጃና ማጠራቀሚያ የለዩ የቤተሰብ ቁጥር |

| ተ.ቁ | የስራ ዓይነት | የስራዎች ተፈፃሚነት ደረጃዎች | | | ስራው የሚመለከታቸው | የማስተማሪያ ዘዴ | መለኪያ ኢንዲኬተር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቀላሉ የሚፈፀሙ | መካከለኛ ተፈፃሚ | ለመፈፀም የሚከብዱ | | | |
| | 1.5 መፀዳጃ ቤት | 1. መጸዳጃ ቤት መሥራት<br>2. የመጸዳጃ ቤት ንጽህና መጠበቅ<br>3. ከተፀዳዱ በኋላ እጅን መታጠብ | ከመጸዳጃ ቤት ጎን የእጅ መታጠቢያ ውኃ ማስቀመጥ | | ማንኛውንም የቤተሰብ አባል | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የልምድ ልውውጥ<br>3. ሰርቶ በማሳየት<br>4. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. የተሰሩ መጸዳጃ ቤቶቸ ብዛት<br>2. በተሰሩት መፀዳጃ ቤቶች የሚጠቀሙ የቤተሰብ አባላት ብዛት<br>3. በተቅማጥ በሽታ የተያዙ ህጻናትቁጥር |
| | 1.6 ተባዮች፣ ቆርጣሚዎችና ተናዳፊዎች | 1. የግል ንፅህና በተ.ቁ<br>1.1.እንደተገለፀው<br>2. ወጥመድን መጠቀም<br>3. ድመትን መጠቀም<br>4. ከዲዲቲ መረጨት ጋር በማይጋጭ መልኩ ቤትን መለቅለቅ መቀባት | 1. የቆሻሻ ማጠራቀሚያን መክደን<br>2. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፀረ ተባይ መድሃኒትን መጠቀም<br>3. የወባ መከላከያ አጎበርን መጠቀም | 1. የቤት አሰራርን ለምስጥ በማይመች መንገድ መስራት<br>2. ለአይጦች መራቢያ ሊሆኑ የሚችሉትን ቦታዎችን ማስወገድ | የቤተሰብ አባላት | 1.የጤና ትምህርት<br>2.የልምድ ልውውጥ<br>3.ሰርቶ በማሳየት<br>4.የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ከቁነጫ፣ ቱኋን፣ ቅማል እና አይጦች ነፃ የሆነ ቤተሰብ ብዛት<br>2. በተባዮች አማካኝነት የሚመጡ ተላላፊ በሽታዎች/ተስቦ፣ ወዘተ/ መቀነስ |
| | 1.7 የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ አወጋገድ | የተሰበሰበ ቆሻሻን ማቃጠልና ማስወገድ ኮምፖስ መጠቀም | 1. የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ መቆፈር<br>2. የፊትና የእጅ መታጠብያ ማዘጋጀት<br>3. የፈሳሽ ቆሻሻ ማስረግያ ጉድጓድ ማዘጋጀት | | ወጣቶችንና ጐልማሳዎችና ሴቶች | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የልምድ ልውውጥ<br>3. ሰርቶ በማሳየት<br>4. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. የቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓድ የሰሩ ቤተሰቦች ብዛት<br>2. በጥቅም ላይ የዋሉ ቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓዶች ብዛት<br>3. የፍሳሽ ቆሻሻ ማስረግያ የሰሩ ቤተሰቦች ብዛት |

| ተ.ቁ | የስራ ዓይነት | የስራዎች ተፈፃሚነት ደረጃዎች | | | ስራው የሚመለከታቸው | የማስተማሪያ ዘዴ | መለኪያ ኢንዲኬተር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቀላሉ የሚፈፀሙ | መካከለኛ ተፈፃሚ | ለመፈፀም የሚከብዱ | | | |
| 2 | የቤተሰብ ጤና ክብካቤ | | | | | | |
| | 2.1 የቤተሰብ ዕቅድ | የቤተሰብ ምጣኔ እውቀትን ማሻሻል | የቤተሰብ ምጣኔ ተጠቃሚዎች መሆን | ይረዥም ግዜ የእርግዝና መከላከያ መጠቀም | ሴቶችና ወንዶች | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የህይወት ልምድ ልውውጥ<br>3. ሰርቶ ማሳየት<br>4. የአቻ ለአቻ ውይይት<br>5. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ከ15 እስክ 49 እድሜ ያሉ ሴቶች ተጠቃሚዎች ቁጥር<br>2. የኮንዶም ተጠቃሚ ወንዶች ብዛት |
| | 2.2 ክትባት | 1. ስለ ክትባት ጠቀሜታ ማወቅ<br>2. ከአንድ ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ህፃናት ማስከተብ | ለእናቶች የሚሰጥ ክትባት ቲቲ | | እናቶችና ህፃናት | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የእናቶች እርስ በርስ መማማር<br>3. ክትባት ለጨረሱ የምስክር ወረቀት መስጠት<br>4. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ዲፒቲ3 የወሰዱ ከአንድ አመት በታች የሆኑ ህፃናት<br>2. ክትባት ያቋረጡ /ድሮፕ አውት ሬት/ ብዛት<br>3. ቲቲ 2 የወሰዱ ሴቶች ብዛት<br>4. ክትባታቸውን ሙሉ ለሙሉ ያጠናቀቁ ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ብዛት |
| | 2.3 የወጣቶች ስነ ተዋልዶ | 1. በቤተሰብ ምጣኔ በኤች አይ ቪ ኤድስና በግብረስጋ ግኑኝነት የሚተላለፉ በሽታዎችንና በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችያለውን እውቀት ማጎልበት<br>2. ስላልተፈለገ እርግዝና ያለውን እውቀት ከፍ ማድረግ | ሱሰኝነትን መከላከልና ማስወገድ ማስተማር | ከጋብቻ በፊት ታቅቦ መቆየት | ወጣቶችንና በጉርምስና እድሜ ያሉትን | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የልምድ ልውውጥ<br>3. የአቻ ለአቻ ውይይት<br>4. ድራማ<br>5. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ስለቤተሰብ ዕቅድ ስለ ኤች.አይ.ቨ/ኤድስ ሌሎች የአባላዘር በሽታዎች ቁጥጥር ላይ የተገኘ ዕውቀት ግንዛቤና የባህሪ ለውጥ<br>2. በግብረስጋ የሚተላለፉ በሽታዎችን መቀነስ<br>3. የቤተሰብ ምጣኔ ተጠቃሚዎች ብዛት<br>4. ያልተፈለገ እርግዝና ያጋጠማቸው ወጣቶች ብዛት |

| ተቁ | የስራ ዓይነት | የስራዎች ተፈፃሚነት ደረጃዎች | | | ስራው በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርገው | የማስተማሪያ ዘዴ | መለኪያ /ኢንዲኬተር/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቀላሉ የሚፈፀሙ | መካከለኛ ተፈፃሚ | ለመፈፀም የሚከብዱ | | | |
| | 2.4 ቅድመ ወሊድ አገልግሎት | 1.የጤና ትምህርት መስጠት<br>• በእርግዝና ወቅት አደገኛ የሆኑ ምልክቶችን መለየት<br>• ለወሊድ ዝግጅት ማድረግ<br>• ቲቲ መስጠት<br>• አይረን መስጠት<br>2. የቅድመ ወሊድ ምርመራና ምክር አገልግሎት | 1 አደገኛ የእርግዝና ምልክት ያለባቸውን እናቶች ለይቶ ወደ ተሻለ የጤና ተቋም መላክ<br>2 ለወሊድ አገልግሎት የሚውሉ ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት | | እናቶችና ሌሎች የቤተሰብ አባላት | 1. በየቤቱ እየዞሩ የሚደረግ የጤና ትምህርት<br>2. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. የተመረመሩ ነፍሰጡሮች ብዛት<br>2. ወደ ሚቀጥለው የጤና ድርጅት የተላኩ ነፍሰጡሮች ብዛት<br>3. አደገኛ የእርግዝና ምልክቶችን የሚያውቁ ብዛት<br>4. አይረን የተሰጣቸው እናቶች ብዛት<br>5. ቲቲ የተሰጣቸው እናቶች ብዛት |
| | 2.5 የማዋለድ አገልግሎት | በሰለጠነ ባለሞያ እቤት ውስጥ ወይም በጤና ድርጅት የወሊድ አገልግሎት ማግኘት | በወሊድ ጊዜ በቤትም ሆነ በጤና ኬላ መውለድ ያልቻሉትን ነፍሰጡሮች ወደሚቀጥለው የጤና ድርጅት መላክ | በጤና ተቋማት መውለድ | እናቶችን | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የልምድ ልውውጥ<br>3. ምክር መስጠት | 1. በህብረተሰብ የጤና ሰራተኞች ወይም በጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች የወለዱ እናቶች ብዛት<br>2. በወቅቱ ተለይተው ወደ ሚቀጥለው የጤና ድርጅት ሄደው የወለዱ እናቶች ብዛት<br>3. በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶች ብዛት |
| | 2.6 የድህረ ወሊድ አገልግሎት | 1. የጤና ትምህርት ስለ ክትባት፣ የቤተሰብ ምጣኔ፣ የእናት ጡትና ስለተጨማሪ ምግብ ጥቅሙ  እና ስለ ጎጂ ልማዶች ማስወገድ<br>2. ቫይታሚን ኤ መውሰድ<br>3. ሕጻናትን የጠዋት ፀሐይ ማሞቅ | 1. የታመሙ ጨቅላ ህፃናትና እናቶችን መለየትና ተገቢውን ህክምና ማግኘት/ ኢንፌክሽንን /መለየት | | እናቶችን | 1. የጤና ትምህርት<br>2. የቴክኒክ እገዛ | 1. የድህረወሊድ አገልግሎት ያገኙ እናቶች ብዛት<br>2. ቫይታሚን ኤ የተሰጣቸው እናቶች ብዛት |
| | 2.7 የህፃናት ተቅማጥ መከላከልና ቁጥጥር | 1. ስለ አካባቢ ንፅህና  የጤና ትምህርት መስጠት<br>2. የታመመ ህፃን በቤት ውስጥ ማከም<br>3. ኦአርኤስ መስጠት | 1. ወላጆች በተቅማጥ ምክንያት ከፍተኛ ፈሳሽ ከሰውነታቸው ያጡ ሕጻናትን መለየትና ወደሚቀጥለው የጤና ድርጅት መላክ | ከአቅም በላይ ከሆነ ሕምምተኛውን ወደ ሚቀጥለው የጤና ድርጅት መውሰድ | እናቶችንና ለአቅም የደረሱ ተንከባካቢዎችና አባቶች | 1. የጤና ትምህርት<br>2. ሰርቶ በማሳየት<br>3. ሕመምተኛን በማየት<br>4. ፖስተርን በማየት<br>5. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. የተቅማጥ መቀነስ<br>2. የታከሙ ተቅማጥ የያዛቸው ህፃናት ብዛት |
| | 2.8 የአጣዳፊ የመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽን ቁጥጥርና ህክምና | ስል በሽታው ምልክቶች መለየት | መመርመርና በቂ ሕክምና ማድረግ<br>ከአቅም በላይ የሆኑ ህፃናትን መለየትና ወደሚቀጥለው የጤና ድርጅተ መላክ | ወላጆች የኒሞኒያን ምልክት አውቀው ልጆቻቸውን ወደሕክምና እንዲወስዱ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ | ወላጆችና ተንከባካቢዎች | 1 የጤና ትምህርት<br>2. በሽተኛን በማየት<br>3. ፖስተርን በማየት | 1.የመተንፈሻ አካላት<br>2. በሽታ ይዟቸው የታከሙ<br>3. ህፃናት ብዛት |

| ተቁ | የስራ ዓይነት | የስራዎች ተፈፃሚነት ደረጃዎች | | | ስራው በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርገው | የማስተማሪያ ዘዴ | መለኪያ /ኢንዲኬተር/ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቀላሉ የሚፈፀሙ | መካከለኛ ተፈፃሚ | ለመፈፀም የሚከብዱ | | | |
| | 2.9 ሥነ ምግብ | 1 የ5 ዓመት ህፃናት የእድገት ክትትል<br>2 ስለተመጣጠነ ምግብ በቂ እውቀት መኖር<br>3. ተገቢ የሆኑ የጡት ማጥባት ተግባራት<br>4. ተገቢ የህፃናት ተጨማሪ ምግብ ሥርዓትን መጠቀም | የህፃናት ተጨማሪ ምግቦች ማዘጋጀት | የጓሮ አትክልት ማልማት | እናቶችንና ህፃናትን | 1 የጤና ትምህርት<br>2 የልምድ ልውውጥ<br>3 እኩያ ከእኩያ ጋር ውይይት<br>4 ሰርቶ በማሳየት<br>5. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. ክብደታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ቁጥር<br>2. እስከ ስድስት ወር ጡት ብቻ የተመገቡ ህፃናት ቁጥር<br>3. እንደተወለዱ በአንድ ሰዓት ውስጥ የእናት ጡት የጀመሩ ህፃናት ቁጥር<br>4.ስድስት ወር ሲሆናቸው ተጨማሪ ምግብ የተጀመረላቸው ህፃናት ቁጥር |
| 3 | በወረርሽኝ የሚስፋፉ በሽታዎችን መከላከንና መቆጣጠር | | | | | | |
| | 3.1 የወባ በሽታን | 1. የጤና ትምህርትና የማነቃቃት ስራን መስራት<br>2. ያቆሩ ውሃዎችን ማፍሰስና መድፈን<br>3. የወባ በሽታን በህብረተሰብ ጤና ሰራተኛ ማከም<br>4. ወረርሽኝ ሲታይ ፈጥኖ ማሳወቅ | 1. የአልጋ አጎበርን መጠቀም | በየሳምንቱ አካባቢን ማፅዳት | አባዎራዎች | 1. የጤና ትምህርት<br>2. ሰርቶ በማሳየት<br>3. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. የአልጋ አጎበር ተጠቃሚ ብዛት<br>2. የተደረጉ አካባቢን የማፅዳት ዘመቻዎች ብዛት |
| | 3.2 ኤች.አይ.ቪ ኤድስና ቲቢን መከላከልና መቆጣጠር | በቂ እውቀት ለማስጨበጥ መስራት | 1. የቲቢ መድሃኒትን በአግባቡ እንዲወስዱ ማድረግ<br>2. ኮንዶምን መጠቀም | የባህሪ ለውጥ ማምጣት | ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል | 1. የጤና ትምህርት<br>2. ሰርቶ በማሳየት<br>3. እኩያ ከእኩያ ጋር ውይይት<br>4. የማሕበረሰብ ውይይት | 1. የኮንዶም ተጠቃሚ ብዛት<br>2. የቲቢ መድሀኒት የሚያቋርጥ በሽተኛ ብዛት<br>3. በህብረተሰቡ ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ ያለው እውቀት ማደግ |

## *12. የጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም የትግበራ ፍሰት*

### ሀ. የአጀማመር ሂደት →

- ወደ ህብረተሰብ መግቢያ መንገድ መፈለግ
- የቀበሌ መስተዳድርና ሕ/ሰብ ጋር በእቅድ ማሳተፍ
- የቀበሌ የጤና ሁኔታን የሚገልፅ ፅሑፍ ማዘጋጀት
- ከአገር ሽማግሌዎች እና ተሰሚነት ካላቸው የቀሌው ሰዎች ጋር ውይይት ማድረግ
- ተከታታይ ቅስቀሳና ትምህርት መስጠት
- ፍላጎትን ማዕከል ባደረገ መልኩ 40-60 ቤተሰብ በአንድ ፓኬጅ መመዝገብ
- ስራ ከመጀመሩ በፊት በሞዴል ቤተሰቦች ቅድመ ትግበራ ጥናት (baseline Survey) ማካሄድ

### ለ. የአተገባበር ሂደት →

የሞዴል ቤተሰቦች ስልጠናና ምረቃ

<u>*የመጀመሪያ ምዕራፍ*</u>

- የግል ንፅህና አጠባበቅ
- የመጸዳጃ ቤት አሠራርና አጠቃቀም
- የንፁህ ውሀ አያያዝና አጠቃቀም
- የእርግዝና ክትትል፣ ወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎት
- የክትባት አገልግሎቶች
- የእናት ጡት ወተት አመጋገብ ሥርዓት
- የቤተሰብ ምጣኔ ዕቅድ አገልግሎት
- የነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች አመጋገብ ሥርዓት
- የጨቅላ ሕፃን ክብካቤ
- ወባን መከላከልና መቆጣጠር/የአጐበር አጠቃቀም፣ የትንኝ መራቢያ ቦታዎች ቁጥጥር ወዘተ...
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር

<u>ሁለተኛ ምዕራፍ</u>

- የምግብ ንፅህና አጠባበቅ
- የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ
- የቤት ንፅህናና የቆሻሻ ማስወገድ ሥራ
- የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻዎች አያያዝና የአወጋገድ ዘዴ
- በራሪ ተባዮችንና ተናዳፊ ነፍሳትን መከላከልና መቆጣጠር
- የተመጣጠነ ምግብ አዘገጃጀትና አመጋገብ
- ለሕፃን የተጨማሪ ምግብ አስፈላጊነት
- የታመመ ሕፃን በቤት ውስጥ ማከምና ወደ ጤና ድርጅት መውሰድ
- የወጣቶች ሥነ ተዋልዶ ጤና
- ቅድመ ጋብቻ ምርመራን ማካሄድ
- የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ጥቅም
- ወረርሽኞችን ማወቅ መከላከልና አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ

<u>ሶስተኛ ምዕራፍ</u>

- የሴት ልጅ ግርዛት
- እንጥል መቁረጥ
- ጥርስና ድድን መቧጠጥ
- ዋግምት
- ያለዕድሜ ጋብቻ

### ሐ. የክትትልና ቀጣይነት ሂደት→

- ክትትል የሚያደረግ አካል መለየትና መወሰን
- ክትትል ማድርግ
- የወርሀዊው ሪፖርት ለቀበሌ መስተዳ ድርና ወረዳ ጤና ጽ/ቤት መስጠት
- የፓኬጁን ስራ አፈፃፀምና ቀጣይነት መገምገም
- በአፈፃፀሙ መሰረት ለጥሩ ስራ ማበረታቻ እውቅና መስጠት

### መ. የማስፋፋት ሂደት

- የማስፋፋት ስራ አግባቦች
- ለማስፋት የሚያግዙ የህብረተሰብ ክፍሎች ለይቶ ማወቅ
- የማስፋፋት ስራና ክትትል ማድረግ
- የማስፋፋት ስራዎችን መገምገም
- በሂደት የተመዘገቡ እድገቶችን በሪፖርት ማቅረብ